# ጊዜው

ቅጽ 5፤ ቁጥር 5

መስከረም 2017



## አሜሪካ፥ እንደ ዘንዶ የሚናገር በግ!

# ከአዘጋጆች ብዕር

በቅርቡ የወጡ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት ሰው ሰራሽ አስተውሎን ወይም አርቲፊሻል ኢንተለጀንስን በመጠቀም የሰው ልጅ ከእንስሳት ጋር መነጋገር እንደሚችል ነው። ይህ ማለት ግን በቅርቡ የሰው ልጅ ከበሬ ጋር ቁጭ ብሎ ስለ ዓለም ሰላም፣ ስለ ኑሮ ውድነት፣ ስለ መካከለኛው ምስራቅ ጦርነት፣ ወዘተ ይነጋገራል ማለት አይደለም።

በዘመናት ሁሉ ከእንስሳት ጋር ቅርርብ ያላቸውና አርቢዎች የጋማ፣ የቤት እንስሳና ከብቶቻቸውን ሲያናግሩና ስሜታቸውን ለመረዳት ሲሞክሩ የኖሩ ቢሆንም ዘመናዊው ሳይንስ ግን የሰው ሰራሽ አስተውሎን በመጠቀም፣ የእንስሳትን የተለያዩ ድምጾች በማቀነባበር እንስሳቱ በሚያወጡት ድምጽ ምን ለማለት ፈልገው እንደሆነ ለመረዳት ይቻላል ነው የሚለው።

መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ ስለሚናገሩ አውሬዎች በተለይ በራዕይ መጽሐፍ ጠቅሶ እናነባለን። እነዚህ እንስሳት አፋቸውን ከፍተው በሚናገሩበት ጊዜ ከማንነታቸው ወይም ተገማች ከሆነው ባሕርያቸው ውጪ የሆነ ነገር ሲናገሩ እንሰማቸዋለን።

ለምሳሌ በራዕይ 13 ሁለት አውሬዎችን ይጠቅስና በተለይ ሁለተኛውን አውሬ በተመለከተ ዮሐንስ ሲናገር በግ ይመስላል ካለ በኋላ ፍጹም ባልተጠበቀ ሁኔታ “እንደ ዘንዶም ይናገር ነበር” ይላል (ራዕይ 13፡11)።

ለመሆኑ ይህ አውሬ ማነው? እንደ ዘንዶ መናገሩስ ምንን ነው የሚያመለክተው? እነዚህን ጥያቄዎች ከመመለሳችን በፊት ግን በመጽሐፍ ቅዱስ የትንቢት ምሳሌ አፈታት መሠረት “አውሬ” ምን ማለት እንደሆነ ማወቅ የግድ ይላል። ከዚያ ሲቀጥል ሌሎቹንም እንዲሁ በመተንተን እግዚአብሔር እንድናውቅ የፈለገውን መልዕክት መረዳት አለብን።

በሌሎች ጉዳዮች ተይዘን ለተወሰኑ ጊዜያት ተቋርጦ የነበረው መጽሔታችን በዚህኛው ዕትሙ ከላይ የጠቀስናቸውን ጉዳዮች የሚያብራራ ይሆናል። **“አሜሪካ፡ እንደ ዘንዶ የሚናገር በግ”** የሚል ርዕስ በሰጠነው በዚህ ዕትማችን አሜሪካ በትንቢት እና በአፈጻጸሙ ላይ ያላትን ተሣትፎ እናብራራለን። ይህ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ዓምዳችን በስፋት የተዳሰሰ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ በጥያቄና መልስ ዓምዳችን ይህንኑ **“አሜሪካ በእርግጥ በትንቢት የተጠቀሰች አገር ናት?”** በሚል መሪ ርዕስ በርካታ ጥያቄዎችን እያነሳን መልሶችን ሰጥተናል። ኑንባቢው ያልተውቴ በሚለው ዓምድ ሥር **“እንደ ዘንዶ”** በሚል መነሻ ሃሳብና ርዕስ ከገዢው ርዕስ ጋር የተያያዘ አጠር ያለ መረጃ ተቀናብሯል።

**“የሥጋ ደዌ ያልበገረው ፍቅር”** በሚል ርዕስ የተወዳጁን ዶ/ር ሮናልድ ኬዘንን ታሪክ አቅርበናል። ዶ/ር ኬዘን ከሕክምና ሙያ ባሻገር ልዩ የሙዚቃ መክሊት የነበረውና ይህንኑ መክሊቱን በተለይ በፍልውሃ ቤተክርስቲያን ብዙዎች የሚያስታውሱት በመሆኑ ዓህ ነው ታሪኪ ዓምድ ይህንን ታላቅ የአገርና የቤተክርስቲያን ባለውለታ ይዘክራል።

በቤተሰብ ዓምዱ ደግሞ **“የትዳር ሥንክሳር”** በሚል ርዕስ ስለ ትዳርና አብረውት ስለሚመጡ ተግዳሮቶች እጥር ምጥን ያለች ጥልቅና ትምህርት ሰጪ ጽሑፍ ቀርቧል።

በኤድን ገነት የመጀመሪያዎቹን ወላጆቻችንን ያሳተውና ዓለምን ሁሉ ለውድቀት የዳረገው **“የቀደመው እባብ፣ ዲያቢሎስ ሰይጣን”** ማንነት Pመዳን ታሪካ ዓምዳችን በስፋት ተንትኖታል።

በዚህ መደበኛ ዕትማችን ከተለመዱት ዓምዶች መካከል Pጥሞና ጊዜ ዓምድ በዚህ ዕትም እንደማይኖር ስንገልጽ ለአንባቢዎቻችን በቅድሚያ ይቅርታ እየጠየቅን ነው።

ይህችን መጽሔት ካነበቡ በኋላ ጥያቄ ወይም ተጨማሪ ማብራሪያ እንዲደረግበት የሚፈልጉት ጉዳይ ካለ በገጽ 3 ላይ በሚገኘው አድራሻችን በአንዱ ሊያገኙን ይችላሉ።

**መልካም ንባብ!**

**አዘጋጆቹ**

# ማውጫ


የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

**አሜሪካ እንደ ዘንዶ የሚናገር በግ** ____ 4

ፆህ ነው ታሪኬ

**የሥጋ ደዌ ያልበገረው ፍቅር** ____ 10

ቤተሰብ

**የትዳር ሥንክሣር** ____ 14

የመዳን ታሪክ

**የቀደመው እባብ ዲያቢሎስ፣ ሰይጣን** ____ 15

ጥያቄና መልስ

**አሜሪካ በእርግጥ በትንቢት የተጠቀሰች አገር ናት?** ____ 19

ኣንባቢው ያለተውቱ

**"እንደ ዘንዶ"** ____ 31


**"ስለዚህ ጊዜው መቼ እንደሚሆን አታውቁምና ተጠንቀቁ፤ ትጉ፣ ጸልዩም" ማርቆስ 13፡33**

**ጊዜው** መጽሔት የመጨረሻው ዘመን መድረሱን ለማስገንዘብና ለማስጠንቀቅ መልዕክት የምታቀርብ እንደመሆኗ የመጽሔቷ ስም ዓርማው ውስጥ ተካትቷል። ከሥሩ የሚታየው ጥሩምባ ከመልዕክቱ በፊት ንቃት እንዲኖር የሚሰማ የማንቂያ ድምጽ ማመላከቻ ነው።


**አዘጋጆች፤**
ድርባ ፈቃዱ
ዳዊት መሐሪ
ዘውዱ ሰብለወርቅ
ጥበበሥላሴ መንግሥቱ

**አምደኞች፤**
ፓ/ር አገኘሁ ወንድም
ፓ/ር መስፍን ማንደፍሮ

**ሽያጭና ስርጭት፤**
ልዝቤ ፈንታሁን
ምንትዋብ ሰብለወርቅ

**Logo, front and back cover design:**
Danny Monnie



**አድራሻ፤**

**ኢሜል፤** editor@giziew.org
**ስልክ: 911-918194 / 911-335790 / 949-611111**
**መ.ሳ.ቁ. 438፤** አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ
Facebook: fb.me/giziew7
**ከአገር ውጪ ለመደወልና ለመጻፍ: +1 314 499-8477**
Whatsapp: **+1 314 499-8477**
Telegram: t.me/**giziew7** ወይም **+1 314 499-8477**
Website: http://www.giziew.org/
YouTube: **@Giziew**


በተለይ እስካልተጠቀሰ በዚህ መጽሔት ውስጥ የተጻፉት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተወሰዱት እኤአ በ1962 ከታተመውና ከአዲሱ መደበኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች ነው።

**የጊዜው መጽሔት ዓላማ፡**
**መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት፤ መድኃኒዓለምን ማዕከል ያደረገ የወንጌል መልዕክት ማቅረብ።**

# ከሜሪካ - እንደ ዘንዶ የሚናገር በግ

ከተቋቋመ ወደ 160 ዓመታት ያሳለፈውና ከሚያመርታቸው ምርቶች መካከል የሕጻናት ዱቄት ወተት አንዱ የሆነው ኔስል የተባለው ኩባንያ በአንድ ወቅት የሚዲያ ትኩረት የሳበ ክስ ቀርቦበት ነበር። ይኸውም የሚያመርተውን የሕጻናት ወተት ወደ 3ኛው ዓለም አገራት እንደ ነርስ በለበሱ የሽያጭ ባለሙያዎች እንዲሰራጭ በማድረግ ሕጻናትን ለከፋ አደጋ አጋልጧል የሚል ነው። እነዚህ የሽያጭ ሰዎች ወደየቤቱ በመሄድ የዱቄት ወተቱን ጥቅም አሳማኝ በሆነ መንገድ በማቅረብ፣ ለእናቶችም በነጻ በመስጠት እንዲሞክሩት ያደርጋሉ። በአብዛኛው ጡት በማጥባት ልጆቻቸውን የሚያሳድጉት እናቶች የተነገራቸውን በማመን ልጆቻቸውን የጠቀሙ መስሏቸው የዱቄት ወተቱን በመስጠታቸው ችግር ውስጥ ይገባሉ።

አንዱ ችግር እናቶቹ ንጹህ ውሃ በማይገኝበት አካባቢ የሚኖሩ በመሆናቸው ዱቄቱን የሚበጠብጡበት ውሃ ልጆቻቸውን ለከፋ ሕመም መዳረጉ ነው። ሁለተኛው ሕጻናቱ የዱቄቱን ወተት ከለመዱ በኋላ የእናታቸውን ጡት በመተው የዱቄት ወተቱ ጥገኛ መሆናቸው ነው። መጀመሪያ የተሰጣቸው ነጻ ጣሳ ዱቄት ካለቀ በኋላ እናቶቹ ሌላ ለመግዛት ውድ ይሆንባቸዋል። ጡት ወደማጥባት እንዳይመለሱ




ሕጻናቱ ሳይጠቡ በቆዩበት ጊዜ ጡታቸው እየደረቀ ከመሄዱ ባሻገር ሕጻናቱ የዱቄት ወተት ስለለመዱ ጡት ወደ መጥባት በፍጹም መመለስ የማይፈልጉ ሆኑ። በመሆኑም ለሕጻናት ዕድገትና መፋፋት እንዲጠቅም በሚል ሽፋን ሲከፋፈል የነበረው ወተት ሕጻናቱን ለመቀንጨር አንዳንዶቹም ለሞት ዳርጓቸዋል።

መልካም መስለው በሚቀርቡ ነገሮች መታለል ያልተለመደ ነገር አይደለም፤ መልካም የተባለውም መልኩን ቀይሮ የጭቃ ጅራፉን ሲመዝና እንደ እባብ መናደፍ ሲጀምር ማስደንገጡ አይቀሬ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ አንድ መልካም መስሎ ስለጀመረና በኋላ ግን መልኩን በመቀየር ከተገመተው ውጪ ሌላ ገጽታ ስለያዘ "አውሬ" በምሳሌያዊ መልኩ ይናገራል።

"ሌላም አውሬ ከምድር ሲወጣ አየሁ፥ የበግ ቀንዶችን የሚመስሉ ሁለት ቀንዶችም ነበሩት እንደ ዘንዶም ይናገር ነበር" ራዕይ 13፡11።

ነገሩ ግራ የሚያጋባ ብቻ ሳይሆን የሚያስፈራም ነው። የበግ የሚመስሉ ቀንዶች ያሉትና በግ ነው ተብሎ ሲጠበቅ የነበረ እንስሳ በሚገርም ሁኔታ ማንነቱ ተቀይሮ "እንደ ዘንዶ" መናገር ይጀምራል። ይህ ከአንድ ጽንፍ ወደሌላው የተፈናጠረው "እንስሳ" በግልጽ የተቀመጠ ነው - ለስላሳና የዋህ ከሚባል በግነት እሣት ወደሚተፋ አስፈሪ ዘንዶነት! ይህንን ትንቢታዊ ምሳሌ ለመረዳት "አውሬ"፣ "ከምድር መውጣት"፣ "የበግ ቀንዶች" እና "ዘንዶ" የሚሉትን በዝርዝር መመልከቱ ጠቃሚ ነው።

በመጽሐፍ ቅዱስ ተምሳሌታዊ (ምልክት) አፈታት መሠረት፤

**"ዘንዶ"** የሚለው ቃል በቀዳሚነት የሚያመለክተው ሰይጣንን ነው። ከዚያ ሲያልፍም በሰይጣን መሪነትና ውክልና የእርሱን ሥራ የሚፈጽሙትንም ቃሉ ያካትታል። "ዓለሙንም ሁሉ የሚያስተው፥ **ዲያብሎስና ሰይጣን** የሚባለው ታላቁ **ዘንዶ** እርሱም የቀደመው **እባብ** ተጣለ፤ ወደ ምድር ተጣለ መላእክቱም ከእርሱ ጋር ተጣሉ" ራዕይ 12፡9። የሚከተሉት ጥቅሶች ደግሞ ተጨማሪ ማብራሪያ ይሰጣሉ፤ ኢሳይያስ 27፡1 እና 30፡6፤ መዝሙር 74፡ 13-14፤ ሕዝቅኤል 29፡3 (እዚህ ጥቅስ ላይ ፈርዖን "ዘንዶ" ተብሏል) እና ኤርምያስ 51፡34።

**"አውሬ"**፤ "**አራተኛይቱ አውሬ** በምድር ላይ **አራተኛ መንግሥት** ትሆናለች" ዳንኤል 7፡23። በዚህ ጥቅስ መሠረት "አውሬ" የሚለው ቃል መንግሥትን ወይም የፖለቲካ ኃይልን የሚያመለክት ነው።

በራዕይ 17፡15 ላይ "አለኝም፦ ጋለሞታይቱ የተቀመጠችባቸው ያየሃቸው **ውኃዎች፥ ወገኖችና ብዙ ሰዎች አሕዛብም ቋንቋዎችም** ናቸው" ይላል። ይህ ጥቅስ "ውኃዎች" የሚለውን ትንቢታዊ ምልክት ሲተነትነው "ወገኖች፣ ብዙ ሰዎች፣ አሕዛብም፣ ቋንቋዎች" በማለት በርካታ ሕዝብ የሰፈረበት ወይም በሕዝብ የተሞላ ቦታ ነው ይላል። በዳንኤል 7፡3 ላይ አራት አራዊት ከባሕር ሲወጡ ዳንኤል እንደተመለከተ ይናገራል። እነዚህም አውሬዎች

ወይም መንግሥታት ከባሕር ወይም ሕዝብ በብዛት ከሰፈረበት ቦታ የወጡ ናቸው። መንግሥታቱም ባቢሎን፣ ሜዶ ፋርስ፣ ግሪክና ሮም ነበሩ (ዳንኤል 2 እና 7፡4-7)። ከዚህ ጥቅስ በመነሳት "ውኃ" ትንቢታዊ ትርጉሙ ብዙ ሕዝብ የሰፈረበትን የሚያመለክት ከሆነ በተቃራኒው "ምድር" የሚለው ቃል ብዙ ሕዝብ ያልሰፈረበትን ቦታ የሚያመለክት ነው በሚለው መተርጎም ይቻላል። ስለዚህ በግ የሚመስለው አውሬ ከምድር መውጣቱ ይህ መንግሥት የሚነሳው ሕዝብ በብዛት ካልሰፈረበት አካባቢ ነው ለማለት እንችላለን።

"ቀንድ" የሚለው ቃል እንደ ዐውዱ በተወሰነ መልኩ ተቀራራቢ ትርጉም ያለው ቃል ነው፤ ይኸውም ኃይላትን፣ ንጉሥን፣ ብርታትን፣ ጥንካሬን የሚያመለክት ነው። ለምሳሌ ዳንኤል 7፡24 ላይ ቀንዶች ነገሥታትን (መሪዎችን) እንደሚያመለክቱ ይናገራል፤ "አሥሩም **ቀንዶች** ከዚያ መንግሥት የሚነሡ አሥር **ነገሥታት** ናቸው"። "ከምዕራብ ወገን አንድ አውራ ፍየል በምድር ሁሉ ፊት ላይ ወጣ፥ ... ለፍየሉም በዓይኖቹ መካከል አንድ ታላቅ ቀንድ ነበረው ... አውራውም ፍየል የግሪክ ንጉሥ ነው፤ በዓይኖቹም መካከል ያለው **ታላቁ ቀንድ** መጀመሪያው **ንጉሥ ነው**" (ዳንኤል 8፡5፣21)። "ዓይኖቼንም አንሥቼ እነሆ፥ አራት ቀንዶች አየሁ። ከእኔም ጋር ይነጋገር የነበረውን መልአክ፦ እነዚህ ምንድር ናቸው? አልሁት። እርሱም፦ እነዚህ ይሁዳንና እስራኤልን ኢየሩሳሌምንም **የበተኑ ቀንዶች** (መንግሥታት፣ ኃይላት) ናቸው ብሎ መለሰልኝ" (ዘካርያስ 1፡18፣19፤ ራዕይ 17፡12)።

ስለዚህ "ሌላም አውሬ ከምድር ሲወጣ አየሁ፥ የበግ ቀንዶችን የሚመስሉ ሁለት ቀንዶችም ነበሩት እንደ ዘንዶም ይናገር ነበር" የሚለውን ትንቢት በዚህ መልኩ ልንፈታው እንችላለን፤ "ሌላም አውሬ (መንግሥት) ከምድር (ሰው በብዛት ካልሰፈረበት ቦታ) ሲወጣ አየሁ፥ የበግ ቀንዶችን የሚመስሉ (የመንግሥቱ መርኾዎች የሆኑ) ሁለት ቀንዶችም ነበሩት፤ እንደ ዘንዶም (እንደ ዲያቢሎስ) ይናገር ነበር" (ራዕይ 13፡11)።

ይህንን በግ የሚመስል አውሬ ማንን እንደሚያመለክት ለመረዳት ከመጽሐፍ ቅዱስና ከታሪክ ጥቂት ነገሮችን መመልከት ያስፈልጋል።

ከዚህ አውሬ በፊት በራዕይ 13 ላይ አንድ ነብር የሚስል ከባሕር የወጣ አውሬ እንዳለ እናነባለን (ራዕይ 13፡1-10)። "አንድም አውሬ ከባሕር ሲወጣ አየሁ፤ አሥር ቀንዶችና ሰባት ራሶች ነበሩት፥ በቀንዶቹም ላይ አሥር ዘውዶች በራሶቹም ላይ የስድብ ስም ነበረ። ያየሁትም አውሬ ነብር ይመስል ነበር፥ እግሮቹም እንደ ድብ እግሮች፥ አፉም እንደ አንበሳ አፍ ነበሩ። ዘንዶውም ኃይሉንና ዙፋኑን ትልቅም ሥልጣን ሰጠው" (ራዕይ 13፡1-2)።

ይህንን አውሬ ይመስላሉ ተብለው የተጠቀሱት አውሬዎች፡- አንበሳ፣ ድብ እና ነብር በዳንኤል 7፡4-8 ላይ የተጠቀሱት ናቸው። እነዚህ የዚያን ጊዜውን ዓለም የገዙ ነገሥታትም አንበሳው ባቢሎንን (612 - 539 ከልደት በፊት)፣ ድቡ ሜዶና ፋርስን (539 - 331 ከልደት በፊት)፣ ነብሩ ግሪክን (331 - 168 ከልደት በፊት)፣ አስፈሪው አውሬ ደግሞ አረመኔውን ሮም (168 ከልደት በፊት - 476 ዓም) የሚያመለክቱ ናቸው። ይኸው የመንግሥታት መዘርዝር በሌላ መልኩ በዳንኤል 2 ላይ በወርቅ፣ በብር፣ በነሐስና በብረት ተብራርቶ እናነባለን።



ከ476 ዓም ጀምሮ እስከ 538 ዓም ባሉት ዓመታት መጽሐፍ ቅዱስ እንደተነበየው ሮምን ተክቶ ዓለምን የገዛ ብቸኛ ኃይል አልነበረም (ዳንኤል 2፡41-44)። ነገርግን በዳንኤል 7፡8 ላይ ከአስፈሪው አውሬ በኋላ ነቢዩ ዳንኤል አስር ቀንዶች እንደወጡና ከእነዚህም ቀንዶች መካከል ሦስቱን ቀንዶች አሽንፎ አንድ ትንሽ ቀንድ እንደወጣ ይናገራል። አሥሩ ቀንዶች የሚያመለክቱት ከሮም በኋላ የተከፋፈሉትን የአውሮጳ መንግሥታት ናቸው፤ እነዚህም በዘመኑ አጠራር ቪዚጎት የተባሉት (ስፔን)፣ አንግሎ-ሳክሰን (እንግሊዝ)፣ ፍራንክ (ፈረንሳይ)፣ አሌማኒ (ጀርመን)፣ በርገንዲያን (ስዊትዘርላንድ)፣ ሎምባርድ (ጣሊያን)፣ ሱዌቪ (ፖርቱጋል)፣ ሔሩሊ (የጠፋ መንግሥት)፣ ኦስትሮጎት (የጠፋ መንግሥት) እና ቫንዳል (የጠፋ መንግሥት) ናቸው። ሦስቱ መንግሥታት ለምን ጠፉ?

ሦስቱ ቀንዶች ሔሩሊ፣ ኦስትሮጎት እና ቫንዳል የጠፉበት ምክንያት ሃማኖታዊና ፖለቲካዊ እንደሆነ በታሪክ ይጠቀሳል። እነዚህ ሦስት መንግሥታት የክርስቶስን ባሕርይ በተመለከተ ለረጅም ጊዜ ከፍተኛ ውዝግብ ውስጥ ገብተው ነበር። ይህ በታሪክ “የአርዮስ ውዝግብ” ተብሎ የሚጠራው ሲሆን ዋናው አቀንቃኝ አርዮስ የተባለ የአሌክሳንደሪያ ግብጽ የነገረመለኮት ሊቅ ነበር። በወቅቱ የሮም ቤተክርስቲያን አስተምህሮውን በምንፍቅና መድባውና አውግዛው የነበረ ሲሆን ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ በ325ዓም በኒቂያ የቤተክርስቲያን በመጥራት ትምህርቱን እንዲወገዝ አስደረገ። አሁን ላይ ሆነን የዚያን ጊዜውን ውሳኔ ስናጠናው ጉዳዩ የክርስቶስን ባሕርይ የተመለከተ ብቻ ሳይሆን አስተምህሮን (ዶክትሪንን) በተመለከተ የመሻርም ይሁን የማጽደቅ ኃላፊነት የማነው የሚለውን በማያወላዳ ሁኔታ ያረጋገጠ ሆኖ እናገኘዋለን። የሮም ቤተክርስቲያን በዘመኑ በነበራት የፖለቲካ ድጋፍ ነገሥታትን ተጠቅማ እነዚህን መንግሥታት እንዲጠፉ ካስደረገች በኋላ አጼ ጁስቲኒያን የሮሙን ሊቀጳጳስ የክርስትና እምነት ጠባቂና “የመናፍቃን አራቂ” የሚለውን የሹመት ስም አጎናጸፋቸው።



ከአስፈሪው አውሬ በኋላ የወጣው ትንሽ ቀንድ በዚህ መልኩ ከአስሩ ቀንዶች (መንግሥታት) መካከል ሦስቱን እንደነቀላቸው ትንቢቱ ይናገራል (ዳንኤል 7፡8)። በመሆኑም ከአራተኛው አውሬ (ከሮም መንግሥት) በኋላ የተነሳና ሦስት ነገሥታትን በመንቀል በምድረ አውሮጳ ኃያል ሆኖ ለ1,260 የትንቢት ቀናት (ራዕይ 12፡6) ወይም ዓመታት የዚያን ጊዜውን ዓለም ሲገዛ የነበረው፣ በሃይማኖት ካባ ተሸፍኖ እንደ መንግሥት አውሮጳን የተቆጣጠረው የሮም ጳጳሳዊ ሥርዓት ነው (በሌላ ስሙ ጳጳሳዊ ሮም ይባላል)። ይህ ከአውሮጳ ነገሥታት ጋር እጅና ጓንት ሆኖ ለዘመናት ሲሠራ የነበረው ኃይልና በራዕይ 13፡1-10 ላይ ከባሕር የወጣው አውሬ አንድና ተመሳሳይ ናቸው።

ይህ ጳጳሳዊ ኃይል አውሮጳን በገናናነት ሲገዛ መቆየቱ የታሪክ ድርሳናት በዝርዝር ያስረዳሉ። በተለይ “የጨለማው ዘመን” ተብሎ በሚታወቀው ጊዜ (538ዓም - 1798ዓም) ይህ ኃይል ከነበረው ሃይማኖታዊ ሥልጣን በተጨማሪ የአውሮጳን ነገሥታት በቁጥጥሩ ሥር አድርጎ ያለ ሮም ሊቀ ጳጳስ ፈቃድ ንግሥናን መቀበል የሚችል ንጉሥ እንዳይኖር እስከማድረግ ደርሶ ነበር። ይህንን ሥልጣኑን የተቀናቀኑትንም ልክ ሲያስገባ እንደነበር ታሪክ ይመሰክራል።

ለአብነትም ያህል በ11ኛው ክፍለዘመን በርዕሳነ ሊቀጳጳስ (ፖፕ) ግሪጎሪ 7ኛ እና አጼ ሔንሪ 4ኛ መካከል የተፈጠረውን ውዝግብ መመልከቱ በቂ ፍንጭ ይሰጣል። በወቅቱ (እኤአ በ1056 ዓም) የስድስት ዓመት ልጅ የነበረው ሔንሪ የጀርመን ንጉሥ ሆኖ ይሾማል። የንግሥና ዘመኑ ከ1056 ዓም ጀምሮ ቢቆጠርም ዘውድ የደፋውና አጼ ሆኖ ብቻውን ማስተዳደር የጀመረው በ1084 ዓም ነበር፤ ከዚያ በፊት የነበሩትን ዓመታት ከእናቱ ጋር በጥምረት ነበር የገዛው። በተለምዶ የጀርመን ነገሥታት የቅድስት ሮም አጼ ተብለው ይሾሙ ስለነበር ሔንሪም ይህንኑ ሥልጣን ተጠቅሞ የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ጳጳሳትን የምሾመውና የምሽረው እኔ ነኝ የሚል መመሪያ ያወጣል።

ይህ የሔንሪ አካሄድ ያልጣማቸው የሮሙ ርዕሳነ ሊቀጳጳስ ግሪጎሪ 7ኛ ትክክል አይደለህም በማለት ደብዳቤ ይጽፉለታል። በወቅቱ እኚሁ ሊቀጳጳስ በታሪክ “የግሪጎሪ ተሃድሶ” የሚባለውንና 27 ነጥቦችን ያካተተ Dictatus papae ("papal dictation") ወይም “የሊቀጳጳሱ የቃል ጽሒፈት” የሚል መመሪያ አውጥተው ነበር። ከእነዚህ 27 ነጥቦች መካከል ጥቂቶቹ የሚከተሉት ይገኙበታል፤ ጳጳሳት መሾምም ሆነ ማውረድ የሚችለው ርዕሳነ ሊቀጳጳስ (ፖፕ) ነው፤ ልዑላን ሁሉ የፖፑን እግሩን ብቻ ነው መሳም የሚችሉት፤ በየአብያተ ክርስቲያናቱ መጠራት ያለበት ስም የሊቀጳጳሱ ብቻ ነው፤ ነገሥታትንና አጼዎችን

ከሥልጣናቸው ማስወገድ የሊቀጳጳሱ ብቻ ሥልጣን ነው፤ ሊቀጳጳሱን ማንም ሊፈርድበት አይችልም፤ ሲኖዶሱን ሳይሰበስብ ሊቀጳጳሱ ጳጳሳትን መሾምም መሻርም ይችላል፤ የሮም ካቶሊክ ቤተክርስቲያን እስካሁን ስህተት ፈጽማ አታውቅም፣ ወደፊትም ለዘላለም ስህተት አትፈጽምም፤ ወዘተ የሚሉ ነበሩ።

ሔንሪ 4ኛ ግን እነዚህን መመሪያና ደንቦች በመቃወም የራሴን ጳጳሳት የምሾመውና የምሽረው እኔ ነኝ በማለት የርዕሳነ ሊቀጳጳሱን (የፖፑን) ሥልጣን ይጋፋል። ይህንን ያልተቀበሉት ግሪጎሪ 7ኛም የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ይጽፉለታል። እርሱም ያንን አልሰማም በማለት ጠንከር ያለ የተቃውሞ ደብዳቤ በምላሹ ይጽፍላቸዋል። በመጨረሻም ሊቀጳጳሱ ሔንሪን ያወግዙትና ከቤተክርስቲያኗ ያስወግዱታል (excommunicate ያደርጉታል)፤ ከዚህ ሌላ በእርሱ ሥር የነበሩትን ዜጎች (አብዛኛዎቹ ካቶሊኮች ናቸው) ከሔንሪ ነጻ መውጣታቸውንና ለእርሱ መታዘዝም ሆነ ግብር መክፈል እንደሌለባቸው ጨምረው ያውጃሉ። በካቶሊክ አስተምህሮ መሠረት በዚህ መልኩ የተወገዘ ሰው ከቤተክርስቲያን መዝገብ የሚፋቅ ብቻ ሳይሆን የመጽሐፍ ቅዱስ ድጋፍ ባይኖረውም ከሰማይም ነው የሚታቀበው ተብሎ ይታመናል። ሁኔታው ያሳሰበውና ዓመጽ ይነሳብኛል ብሎ የሰጋው ሔንሪም ይቅርታ እንዲጠይቅ በተደረገበት ተጽዕኖ ምክንያት ሊቀጳጳስ ግሪጎሪ 7ኛን ይቅርታ ሊጠይቅ በአስከፊው የአውሮጳ ክረምት የሦስት ቀን ጉዞ ወደ ሮም ያደርጋል። በወቅቱ ሊቀጳጳሱ ካኖሳ በተባለች ሰሜናዊ የጣሊያን ከተማ ይገኙ ስለነበር እዚያ ድረስ ይሄዳል፤ ጉዞውም በታሪክ "የካኖሳው ጉዞ" ተብሎ ይጠራል።

ሔንሪ እዚያ እንደደረሰ ፖፕ ግሪጎሪ 7ኛ ወዲያው ሊቀበሉት ስላልፈለጉና እርሱን አዋርደው በመላው አውሮጳ ለሚገኙት ነገሥታት ትምህርት የሚሆን መልዕክት መላክ ስለፈለጉ፤ አጼ ሔንሪ ይቅርታ እየለመነ በአስከፊው ብርድና በረዶ ውጪ እንዲቆይ አደረጉት። በመጨረሻም ጫማውን አውልቆ በባዶ እግሩ በበረዶ ላይ ሆኖ ወደ ሊቀጳጳሱ እንዲገባና እግራቸውን በመሳም ይቅርታ እንዲማጸን አስደረጉት።




ይህ ጳጳሳዊ ሥልጣን በዚህ መልኩ በገናናነት ቢቀጥልም እስከመጨረሻው ግን አልዘለቀም። በአውሮጳ ኃያል ሆኖ የተነሳው ናፖሊዮን ቦናፓርት ይህንን ለ1,260 ዓመታት ተንሰራፍቶ የቆየውን የሮም ሊቀጳጳስ ሥልጣን የሚገታ ተግባር ፈጸመ። ለዘመናት የቆየውን የሮም ሊቀጳጳስ ንጉሥን የመሾም ሥልጣን ናፖሊዮን በመቃወምና ማንም ከእርሱ በላይ እንዳልሆነ ለማሳየት ራሱን አጼ በማድረግ ዘውድ በራሱ ላይ ደፋ። ይህ ብቻ ሳይሆን የጦር አዛዡን ጄኔራል በርቲየርን በመላክ እኤአ በ1798 ዓም በወቅቱ ሥልጣን ላይ የነበሩት ሊቀጳጳስ (ፖፕ) ፓየስ 6ኛ የተባሉትን ከሥልጣናቸው በማንሳት ወደ ፈረንሳይ በግዞት ላካቸው። ከ18 ወራት በኋላ እርሳቸውም በግዞት እያሉ አረፉ።

ይህ ለ1,260 ዓመታት ሰፍኖ የቆየው ጳጳሳዊ ሥርዓት በዚህ መልኩ ሲዳከም ወይም በራዕይ 13፡3 መሠረት “ለሞት የሚያደርስ ቊስል” ከተቀበለ በኋላ በዚያው ዘመን አካባቢ ስለተከሰተ ነገር ራዕይ 13፡11 እንዲህ ይላል “ከዚያም ሌላ አውሬ ከምድር ሲወጣ አየሁ፤ እርሱም እንደ በግ ሁለት ቀንዶች ነበሩት፤ ነገር ግን እንደ ዘንዶ ይናገር ነበር”። ይህ “አውሬ” ወይም መንግሥታዊ ኃይል ከበርካታ ማንነቱ በተጨማሪ በተለይ የሮም ጳጳሳዊ ኃይል በተዳከመበት ወቅት፣ ሕዝብ በብዛት ካልሰፈረበት ወይም “ከምድር” የወጣ መሆኑና አጀማመሩ እንደ በግ ጉዳት የማያደርግ ለስላሳና መልካም መሆኑና ሁለት ቀንዶች የነበሩት መሆኑ ልዩ መለያዎቹ ናቸው ። እነዚህን መለያዎች ይዘን በ18ኛው ክፍለዘመን መጠናቀቂያ አካባቢ በዓለም ላይ የተነሳ ኃይል ማነው ብለን ብንጠይቅ ከአሜሪካ ሌላ የምናገኘው የለም። (ለአብነት ያህል አሜሪካ በተመሠረተችበት ጊዜ የሕዝቧ ቁጥር 2.5 ሚሊዮን ብቻ ነበር። በአሁኑ ጊዜ (በ2024) የአሜሪካ ሕዝብ ቁጥር ከ332 ሚሊዮን በላይ ነው።)



አሜሪካ ከአነሳሷ በጣም ሰላማዊ አገር ነበረች። በእርግጥ ወደ አዲሷ ምድር የመጡት አውሮጳውያን በአሜሪካ ይኖሩ በነበሩት ተወላጅ ሕንዶች (ሬድ ኢንዲያንስ) ላይ እጅግ የከፋ መከራ ቢያደርሱም አሜሪካ አነሳሷ ግጭት የወለደው አይደለም፤ በአብዛኛው ሰላማዊ የሚባል ነበር። በተለይ በአውሮጳ ይካሄድ የነበረው የሃይማኖት መብት ረገጣ ያስመረራቸው ወደ አዲሱ አገር ተሰድደው በመምጣት የመሠረቷት ከመሆኗ አንጻር አሜሪካ የክርስቲያን (የፕሮቴስታንቶች) አገር እንድትሆን አድርጓል። ይህም ክርስቲያናዊ እሴት በሕገ መንግሥቱም ሆነ በአጠቃላይ የአገረ መንግሥት ምሥረታ ላይ ትልቅ ተጽዕኖ አሳድሯል።

የታሪክ ምሑራን እንደሚሉት ወደ አሜሪካ መጥተው አገር የመሠረቱት ሰዎች የአውሮጳው ጳጳሳዊ አገዛዝ ከመንግሥት ጋር በመተባበር ያደረሱባቸውን ግፍ በመቃወም ስለነበር እንደ መፈክር ያነገቡትና የሚከተሉት መርኽ “ሃይማኖት ያለ ጳጳስ፤ አገር ያለ ንጉሥ” የሚል ነበር። በምትኩ ፕሮቴስታንታዊነት እና ሪፓብሊካዊነት ዋንኞቹ መርኾዋቸው ሆኑ። ይህም ከምድር በወጣው በግ ሁለት ቀንዶች ተመስሎ እናነባለን፤ “ሌላም አውሬ ከምድር ሲወጣ አየሁ፥ የበግ ቀንዶችን የሚመስሉ ሁለት ቀንዶችም ነበሩት” (ራዕይ 13፡11)።

ይህ አውሬ በግ መሆኑ አጀማመሩ ሰላማዊና ንጽሕናን የተላበሰ መሆኑን የሚያመላክት ነው። የአሜሪካ የነጻነት ድንጋጌ (ዴክላሬሽን ኦቭ ኢንዲፔንደንስ) እንዲህ ይላል “ሰዎች ሁሉ ነጻ እና እኩል ሆነው መፈጠራቸውን፤ አንዳንድ የማይገሰሱ መብቶች እንደተሰጧቸው፤ ከእነዚህም መካከል ሕይወት፣ ነጻነት እና ደስታን መሻት መሆናቸውን፤ እነዚህም እውነቶች ለራሳቸው ምስክር እንደሆኑ እናምናለን” የሚል ነው። ከዚህ አንጻር ሃይማኖት በፕሮቴስታንታዊ መርኽ መንግሥት ደግሞ በሪፓብሊክ ወይም በሕዝብ ውክልና የሚተዳደር መሆን አለበት በሚል ገና ከጅምሩ የአገረ መንግሥት ምሥረታው መነሻ ሃሳብ የሆነው። ይህ ንጽሕና ግን እንደተባለው አይቀጥልም፤ ይህንኑ በግ መሰል አውሬ “እንደ ዘንዶም ይናገር ነበር” ይላል (ራዕይ 13፡11)።

በመጽሐፍ ቅዱስ “በግ” የክርስቶስ ተምሳሌት ሆኖ ነው የምናነበው (ዮሐንስ 1፡29)። በራዕይ 13፡11 የተጠቀሰው ግን በግ ብቻ ሳይሆን “አውሬም” ነው። ከዚያ ሲያልፍ የሚናገረው “እንደ ዘንዶ” ነበር (ራዕይ 13፡11)። ይህ በጣም አሳሳችና አምታች የሆነ ባሕርይ ያለው በግ መሆኑ ያሳየናል። እንደ ቤት እንስሳ በግ ነው ተብሎ ሲጠበቅ አውሬ ነው፤ ከዚያ ሲያልፍ ደግሞ እንደ ዘንዶው ማለትም እንደ ዲያቢሎስ፣ ሰይጣን ወይም በኤደን ገነት ሔዋንን እንዳሳሳታት እባብ አሳሳች ነው።

በብሉይ ኪዳን ነቢያት የእግዚአብሔር አፍ ሆነው ያገለግሉ እንደነበር ይህም በግ የዘንዶው አፈቀላጤ ሆኖ እናየዋለን። በዚህም ምክንያት ይህንን ከምድር የወጣውን አውሬ በሌሎቹ የራዕይ መጽሐፍ ክፍሎች “ሐሰተኛ ነቢይ” በማለት ይጠራዋል (ራዕይ 16፡13፤ 19፡20፤ 20፡10)። ሔዋን የተሳሳተችው ከእባቡ

ይወጣ በነበረው ንግግር ነበር (ዘፍ. 3፡1-5)። ይህ በበግ የተመሰለው አውሬም የዘንዶው አፍ በመሆን ቀልብን የሚስቡና የሚማልሉ ነገሮችን በመናገር እውነትን ይበርዛል፤ ሐሰትን ይነዛል፤ በክርስትና ስም ክርስትናን ያበላሻል፤ ሰዎችንም ያስታል። ከዚህ ሲያልፍም "ለሞቱ የሆነውም ቍስል ተፈወሰለት ለፊተኛው አውሬ (ጳጳሳዊ ሥርዓት) ምድርና በእርሱ የሚኖሩት እንዲሰግዱለት ያደርጋል" (ራዕይ 13፡12)።

የነጻነትና የዴሞክራሲ ፋናወጊ የሆነችው አሜሪካ በዚህ ልክ በመውረድ የሃይማኖትን ነጻነት ከሰዎች በመንፈግ አስገዳጅ ሕጎችን ታወጣለች ብሎ ማመን ሊከብድ ይችላል። ሆኖም ግን የአሜሪካንን ፖለቲካ በቅርብ ለሚከታተል ይህ ሁኔታ በተግባር እየተፈጸመና ሥር እየሰደደ የመጣ እንደሆነ ለመረዳት አያዳግትም። ዙሩ እየከረረ ሲሄድም የሃይማኖት ነጻነት አጥተው የነበሩትን ያስጠለለችው አሜሪካ መልኳን በመቀየር ለመጀመሪያው አውሬ (ጳጳሳዊ ሥርዓት) ምስል በማቆም ወይም አስገዳጅ ሃይማኖታዊ ሕግጋትን ታወጣለች ይለናል ራዕይ 13፡ 14። ይህ በአሜሪካ (ሐሰተኛው ነቢይ) የተመሰለው በግ መሰል አውሬ ለመጀመሪያው አውሬ ሲል የሚያወጣውን ትዕዛዝ ሰዎች በእጃቸው (ለመኖር ሲሉ) ወይም በግምባራቸው (አምነውና ፈቅደው) ምልክት እንዲቀበሉ ያስገድዳቸዋል (ራዕይ 13፡16)። አንቀበልም የሚሉትን ያሳድዳል፤ የሞት አዋጅም ያውጃል (ራዕይ 13፡15)።

ሃሳቡን ጠቅለል ለማድረግ ከምድር የወጣው በአሜሪካ የተመሰለው በግ መሰሉ አውሬ እንደ ዘንዶ መናገር በሚጀምርበት ጊዜ አራት ነገሮች ይከሰታሉ፤

**1.** "በፊተኛውም አውሬ ሥልጣን በእርሱ ፊት ሁሉን ያደርጋል" (ራዕይ 13፡12)። ከባህር የወጣው አውሬ የሮም ጳጳሳዊ ሥርዓት እንደነበር ተመልክተናል። ይህ ኃይል የጨለማው ዘመን በሚባለው የመካከለኛው ዘመን በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ክርስቲያኖችን አሳድዷል ፤ገድሏል። ልክ እንደዚህ አሳዳጅ ኃይል አሜሪካም እንደ ዘንዶው መናገር ስትጀምር ሰዎችን ወደ አስገዳጅ ሃማኖታዊ ሥርዓት ታስገባለች፤ እምቢ የሚሉትንም ታሳድዳለች።

**2.** "ለሞቱ የሆነውም ቍስል ተፈወሰለት ለፊተኛው አውሬ ምድርና በእርሱ የሚኖሩት እንዲሰግዱለት ያደርጋል" (ራዕይ 13፡12)። አሜሪካ የዓለም መንግሥታትን በመምራት ሐሳዊ ክርስቶስ ለሆነው የጳጳሳዊ ኃይል እንዲሰግዱ ወደማስገደድ ሥራ ውስጥ ትገባለች። (ሐሳዊ ክርስቶስ ማለት ሐሰተኛ ወይም ጸረ ክርስቶስ ማለት ብቻ ሳይሆን የክርስቶስ ቦታ ለኔ ይገባኛል ማለትም ነው)።

**3.** "የሰይፍም ቍስል ለነበረውና በሕይወት ለኖረው ለአውሬው ምስልን እንዲያደርጉ በምድር የሚኖሩትን ይናገራል" (ራዕይ 13፡ 14)። አሜሪካ ከባህር ለወጣውና ቁስሉ ለተፈወሰለት አውሬ (ጳጳሳዊ ሥርዓት) ሃይማኖታዊ ሕግጋትን ትደነግጋለች። የጨለማው ዘመን በሚባለው ወቅት ዓለምን ሲቆጣጠር በነበረው ጳጳሳዊ ሥርዓት ዘመን እንደነበረው አሁንም እንዲሁ ሃይማኖትን ከመንግሥት ጋር በማጋባት አሜሪካ ምስለ ጳጳሳዊ ሥርዓትን ትዘረጋለች።

**4.** "ለአውሬውም ምስል የማይሰግዱለትን ሁሉ (ያስገድላቸዋል)" (ራዕይ 13፡15)። ዓለምን በኃያልነት የምትመራው አሜሪካ ለዚህ ለጳጳሳዊ ሥርዓት የሚቆመውን ምስል "አንቀበልም"፣ "አንሰግድም" የሚሉ ሁሉ እንዲገደሉ የዓለምን መንግሥታት ታስተባብራለች። የዓለም መንግሥታትም አንታዘዝም ባዮችን ለመግደል የሚያስችል የሞት አዋጅ ያውጃሉ። (ዝርዝር መረጃ በጥያቄና መልስ ዓምዳችን ገጽ 19 ይገኛል)

በመጨረሻው ዘመን ሰዎች ከሁለት በአንዱ ጎራ እንዲሰለፉ የሚያደርጋቸው ዋና ጉዳይ አምልኮ ይሆናል። ይህ ደግሞ በሰማይ የጀመረ እንደሆነ ኢሳይያስ 14 እና ሕዝቅኤል 28 ይነግሩናል። ሉሲፈር የእግዚአብሔርን ዙፋን አጥብቆ ተመኘ፣ አምልኮና ስግደት የሚገባኝ ለእኔ ነው አለ። ኃይሉን ሲያስተባብር ከመላዕክት ሲሶውን አታላይ በሆነው ችሎታው ተጠቅሞ ከእርሱ ጋር እንዲሆኑ አሳመናቸው። ይህንኑ የማሳሳቻ ስልት ተጠቅሞ ሔዋንን ካታለለ በኋላ የዚህች ምድር ገዢ እንደሆነ አደርጎ ራሱን ቆጠረ። በመጨረሻው ዘመንም ስግደትና አምልኮ የሚገባው ለኔ ነው በሚል አንታዘዝም በሚሉት ላይ እርምጃ ይወስዳል።

ስግደት ማን እንደሚገባው ቃሉ ሲነግረን፤ "የፍርዱ ሰዓት ደርሶአልና እግዚአብሔርን ፍሩ ክብርንም ስጡት፤ ሰማይንና ምድርንም ባሕርንም የውኃንም ምንጮች ለሠራው ስገዱለት" ይላል (ራዕይ 14፡7)።

**ጥበበሥላሴ መንግሥቱ**

# የሥጋ ደዌ ያልበገረው ፍቅር

አንድ እሁድ ከሰዓት፣ አዲስ አበባ ውስጥ ሰበታ መንገድ ላይ በሚገኘው አለርት ሆስፒታል ጊቢ የሚኖረውን ጓደኛዬን ለመጠየቅ ሄድኩ። በጊዜው ሁለታችንም የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ነበርን። በጊቢው ውስጥ ብስክሌት እያሽከረከርን ስንዝናና ድንገት ዕድሜያቸው ከአስር የማይበልጥ አራት ልጆች ወደኛ አቅጣጫ እየሮጡ መጡ።

የልጆቹ ድምፅ ሸካራና ጎርናና ነበር። ሲጠጉን ሁሉም የራስ ፀጉርና ቅንድብ የሌላቸው፣ አፍንጫዎቻቸውና እጆቻቸው የተሸራረፉ መሆናቸውን ሳይ በድንጋጤ ፍሬን ያዝኩ። ከፊቴ ገጽታ መደንገጤንና መከፋቴን የተገነዘቡት ሕፃናት ዞረው ወደ መጡበት ተመለሱ።

ልጆቹ የሥጋ ደዌ ሕሙማን ነበሩ። ይህ ከባድና ተላላፊ ደዌ የሚጎዳው ቆዳን፣ አፍንጫን፣ ላንቃና ዓይኖችን ሲሆን፣ በሽታውን የሚያዛምተው ባክቴሪያ የስሜት ሕዋሳትንም ይገድላል። የበሽታው ሰለባዎች የእጅና የእግር ጣቶቻቸውም እየተበሉ ያልቃሉ።

የአለርት ሆስፒታል በሥጋ ደዌ የሚሰቃዩ ሰዎችን ለማከም የተዘጋጀ ቦታ መሆኑን አውቅ ነበር። በዕድሜ የሚቀርቡኝ የበሽታው ጉዳተኞች ማየቱ ግን ቀፎኝ ነበር። ልጆቹ ከእኔ ጋር መጫወት ፈልገው እንደቀረቡኝ የገባኝ እጅግ ቆይቶ ነው። ሳላውቀው ለሰው ልጆች መስጠት ያለበትን ርኅራኄ ነፍጌያቸው እንደነበር ዛሬ ሳስብ በእጅጉ አዝናለሁ።

ከጥቂት ዓመታት በኋላ ሮላንድና በርጊታ ኬዘን (Roland and Birgitta Kazen) ከሚባሉ




ስዊድናዊያን ባልና ሚስት ጋር ተዋወቅሁ። ይኖሩ የነበረው የሥጋ ደዌ የሚሰቃዩ ሕፃናትና አዋቂዎች በሚታከሙበትና በሚያድሩበት አለርት ጊቢ ውስጥ ነው። የተገናኘነው ደግሞ ሮላንድ ሙዚቃ በሚጫወትበትና መዘምራን በሚያሰለጥንበት በፍልውሃ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተክርስቲያን ነበር።

ሮላንድና በርጊታ ኢትዮጵያ የገቡት የሥጋ ደዌ ታማሚዎችን ለመርዳት መሆኑን ጥቂት ቆይቼ ሰማሁ። ስለ በሽታው ብዙ ከማወቃቸው በፊት ሮላንድ በስዊድን አገር ሐኪም ሆኖ ያገለግል ነበር። ከዚያም በ1975 (እኤአ) ወደ ሴራሊዮን አገር ሄዶ ማሳንጋ ሆስፒታል ተብሎ በሚጠራው የሥጋ ደዌ ሐኪም ቤት በመሪነት እንዲሠራ ተጠራ።

ጥሪውን ከመቀበላቸው በፊት ሮላንድና በርጊታ ስለ በሽታው አሰቃቂ ባሕሪዎች ጥናት አደረጉ። በሥጋ ደዌ ምክንያት እጅና እግሮቻቸው መንቀሳቀስ ያቃታቸው ሕሙማን በቀዶ ጥገናና በሌሎች የሕክምና ዘዴዎች መጠነኛ መሻሻል ሊያሳዩ እንደሚችሉ ተገነዘቡ። ሮላንድ የቀዶ ጥገና ሐኪም ስለነበር ጥሪውን ለመቀበል ወስነው፣ ስዊድን የነበረውን ቤታቸውን ሸጡና ሻንጣዎቻቸውን ሸክፈው ከሦስት ወጣት ልጆቻቸው (ቶማስ፣ አኔታ፣ እና ማግነስ - Thomas, Agneta and Magnus) ጋር ወደ ሴራሊዮን በረሩ።

በማሳንጋ ሆስፒታል ሮላንድ፣ በርጊታና ልጆቻቸው የሥጋ ደዌ ህሙማንን በመርዳት ሙሉ በሙሉ ተጠመዱ። ሮላንድ ቀዶ ጥገና ሲሰራ ሴት ልጁ በጥንቃቄ ፎቶ ታነሳ ነበር። ፎቶግራፎቹን ሮላንድ ሐኪሞችን ለማስተማር ይጠቀምባቸው ነበር። የቀሩት ልጆቻቸው ጧት ትምህርታቸውን ከጨረሱ በኋላ መጫወቻዎቻቸውንና የሕፃናት መጽሐፍት ወስደው የሥጋ ደዌ ከያዛቸው ልጆች ጋር ይጫወቱ ነበር።

አሁን ላይ ስጠይቃት በሴራሊዮን ያሳለፏት ጊዜ የሕይወታቸው እጅግ አስደሳች ዓመታት እንደነበሩ በርጊታ ነግራኛለች። ሮላንድ ሥራውን አብዝቶ ይወድ ነበር። ታማሚዎቹን ስለሚወድ እነርሱም ይወዱት ነበር። ከዚህ ባሻገር ሮላንድ በቀዶ ጥገና አዳዲስ አሠራሮች ስለፈጠረ ከእርሱ ለመማር

ሐኪሞች ከጎረቤት አገራት ወደ ማሳንጋ ሆስፒታል ይሄዱ ነበር።



በሕክምና ያገገሙትን የሥጋ ደዌ ተጠቂዎች የሚረዱበትን መንገድ ማመቻቸት ደግሞ የበርጊታ ኃላፊነት ነበር። ከሐኪም ቤት ታክመው የወጡ ወጣቶች ለሁለት ዓመታት የአናጢነት፣ የልብስ ስፌት ወይም የግብርና ትምህርት ይሰጣቸው ነበር። ትምህርቱን ሲያጠናቅቁ ልብስ መስፊያ መኪናዎች ወይም የተለያዩ መሣሪያዎች ተሰጥቷቸው ወደየ አገር ቤታቸው ተመልሰው በተማሩት ሙያ አዲስ ሕይወት እንዲጀምሩ ይደረግ ነበር።

በርጊታ በሥጋ ደዌ ምክንያት ከባሎቻቸውና ከዘመዶቻቸው ለተገለሉ ሴቶች የተለየ ዕቅድ ነበራት። እነዚህ ሴቶች ከሐኪም ቤት ሲወጡ አነስተኛ የንግድ ሥራ እንዲጀምሩ ሩዝ፣ ዘይትና ስኳር እንዲሰጣቸው ታርግ ነበር። በዚህም የሥጋ ደዌን እንደ ሞት መቅሰፍት ይቆጥሩ የነበሩ ዘመዶቻቸውም ያገለሏቸው ሴቶች ላይ መንፈሳዊና ኢኮኖሚያዊ መሻሻል ሊያሳዩ ችለዋል። ይህም ሴቶቹ ከኖሩበት ማኅበረሰብ ጋር ተመልሶ የመቀላቀል በር ከፍቶላቸዋል።

በርጊታ ግን በዚህ አላቆመችም። እናት አባት ለሌላቸው የሥጋ ደዌ ተጠቂ ሕፃናት ብዙ ትጨነቅ ነበር። ስላዘነችላቸውም ቤትና ትምህርት ቤት እንዲሠራላቸውአደረገች።



በመጨረሻም ሮላንድ እና በርጊታ በማሳንጋ ለአስራ አራት ዓመታት ካገለገሉ በኋላ ሮላንድ አዲስ አበባ ካለው አለርት ሆስፒታል የሥራ ጥሪ ደረሰው። ይህ ዓለምአቀፋዊ ተቋም፣ ከፍተኛ የሥጋ ደዌ ሕክምናና የቀዶ ጥገና የሚደረግበት ቦታ ነው። በተጨማሪ ከኢትዮጵያና ከዓለም ዙሪያ የተውጣጡ ሐኪሞች ምርምር የሚያደርጉበትና የሚሰለጥኑበት ቦታ ነው። ሮላንድ የማከምና የማስተማር ሥራውን በአለርት ሲቀጥል፣ በርጊታ ደግሞ የዓለም አቀፍ ሥልጠና ኃላፊ ሆነች።

በሥጋ ደዌ ሕክምና ሮላንድ ከፍተኛ ዕውቅና ነበረው። ቤተክርስቲያን ውስጥ ግን ራሱን ዝቅ አድርጎ የሚተጋ መንፈሳዊ ሰው ነበር። የእርሱና የበርጊታ ትኩረት አገልግሎት ላይ ስለነበር ስለሥራቸው የማውራትና ራሳቸውን የማግነን ጥማት አልነበራቸውም።



ሁለቱም ለወጣቶች አስገራሚ ፍቅር ነበራቸው። በተለይም የትምህርት ፍቅር ወይም የሙዚቃ ዝንባሌ ላላቸው ሁሉ ልባቸው ክፍት ነበር። መልካም ምክር ከመለገስ ጀምሮ ባላቸው ዓቅም የተቸገሩ የቤተክርስቲያን ወገኖችን እስከ መርዳት ድረስ ራሳቸውን የሰጡ መልካም ክርስቲያኖች ነበሩ።

ሮላንድና በርጊታ ከአውሮጳ መጥተው የባሕላቸውንና የማንነታቸውን የበላይነት ለማስረጽ እንደሚታገሉ ፈረንጆች አልነበሩም። ባገኙት አጋጣሚ ክርስትና በኢትዮጵያ ባህልና ቋንቋዎች እንዲዳብር የበሰለ ጥረት ያደርጉ ነበር። በተለይም መዝሙሮች በአገር በቀል ቅኝቶች እንዲጻፉና እንዲዘመሩ በማበረታታት ብዙ ለስኬት የበቁ ሥራዎችን ሠርተዋል።

ጡረታ ከወጡ በኋላ ሮላንድና በርጊታ ወደ ትውልድ አገራቸው ስዊድን ተመለሱ። እዚያ እያሉ በስካይፕ

አውርተን ነበር። ያኔ ሮላንድ ኢትዮጵያ መመላለሱን እንዳላቆመና ወደ ታንዛኒያም በተደጋጋሚ እንደሚሄድ ነግሮኝ ነበር።

“ጡረታ ወጥተህ የለም እንዴ?” ስለው ፈገግ ብሎ “ጡረታ ስለወጣሁ የማስተዳደር ኃላፊነት የለኝም። ይህ ደግሞ የምወደውን ለማድረግ ነጻነት ይሰጠኛል። ወደ ኢትዮጵያና ወደ ታንዛኒያ የምሄደው ሐኪሞችን ለማስተማር ነው። በተጨማሪ ከወዳጆቼ ጋር በሥጋ ደዌ ቀዶ ጥገናን አስመልክቶ አንድ የትምህርት መጽሐፍ እየጻፍን ነው። ይህን የምናደርገው እኛ በሌለንበት ታማሚዎቹ እንዳይጎዱ ነው” በማለት ነበር የመለሰልኝ።

ይህንን ባወራን በሦስት ዓመቱ ሮላንድ በጠና ታመመ። በርጊታ እንደነገረችኝ እሷና ልጆቻቸው ከብበውት ሲዘምሩ ሮላንድ ወደ ላይ ጠቁሞ በለሆሳስ፤ “ክርስቶስን ተከተሉት” ይል ነበር። ብዙም ሳይቆይ ከዚህ ዓለም ድካም በጌታ አረፈ።







የሮላንድና የበርጊታ ሕይወት በፍቅር ቀለም የተጻፈ ወንጌል ነው። በሙያው ገንዘብ ማካበትና ዝነኛ መሆን ቢፈልግ ሮላንድ አውሮጳ መቅረት ወይም ወደ አሜሪካ መጓዝ ይችል ነበር። እርሱና ሚስቱ ግን የተሻለ ዋጋ ያለውን ሰማያዊ አገልግሎት መረጡ።

“ሙሴ ካደገ በኋላ፣ የፈርዖን የልጅ ልጅ መባልን በእምነት እምቢ አለ። ለጥቂት ጊዜ በኀጢአት ከሚገኝ ደስታ ይልቅ፣ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር መከራን መቀበል መረጠ። ከግብፅ ሀብት ይልቅ ስለ ክርስቶስ መከራን መቀበል እጅግ የሚበልጥ ሀብት መሆኑን ተገነዘበ፤ ወደ ፊት የሚቀበለውን ብድራት ከሩቅ ተመልክቶአልና። የንጉሡን ቍጣ ሳይፈራ ግብፅን ለቆ በእምነት ወጣ፤ የማይታየውንም እንዳየው አድርጎ በመቍጠር በሐሳቡ ጸና” (ዕብራውያን 11:24-27)።

እንደ ጥንቱ ሙሴ ብድራቱን ከሩቅ የተመለከቱት ሮላንድና በርጊታ ድሎት የሞላበትንና የሚሞቀውን ቤታቸውን ሽጠው ወደ ማያውቁት አገር ሄዱ። ሆኖም በዕውር ድንበር አልተጓዙም። ሴራሊዮን ሲደርሱ የተቀበላቸው መድኃኒዓለም ስለ ሥጋ ደዌ በጥልቅ ያውቃል። ለምጻሞችን በገሊላ ይዳስስና ይፈውስ የነበረው ጌታ ለሮላንድ አዳዲስ የቀዶ ጥገና ጥበብ ሰጠው። ጌታ ክርስቶስ ጥንት ለምጻሞች ከፈወሰ በኋላ ወደ ቤታቸው በደስታ እንዲመለሱ ያደረግ ነበር። በዚያው ደግነቱ ደግሞ በአፍሪቃ ታመው የኑሮ መመሳቀል ያስጨነቃቸውን በማቋቋም ሥራ ላይ በርጊታን አሰማራት።

ወደ ኢትዮጵያ ሮላንድና በርጊታ ያመጡት የሚታይና የሚጨበጥ ርኅራኄ ነው። ላገኙት ሰው ሁሉ ይሰጡ የነበረው ክብረት የሰማይ አምላክ ቅርብ መሆኑን እንዳይ አድርጎኛል። ከሁሉ በላይ እኔ ለፈራኋቸው የሥጋ ደዌ ሕሙማን ያሳዩት ፍቅር፤ የጽድቅ ፍሬ በዚህች ጨለማ ምድር ላይ መለምለም እንደሚችል መተዛዘን ላቃተን ሁሉ ያስተምራል።

ሮላንድና በርጊታ ከሦስቱ ልጆቻቸው በተጨማሪ ከኢትዮጵያ ከመልቀቃቸው በፊት ጁሱፉ (adopted son Jusufu) በሚባል ተጨማሪ ልጅ በጉዲፈቻ ተባርከዋል። ከአራቱ ልጆቻቸው 10 የልጅ ልጆችና 2 የልጅ ልጅ ልጆች አፍርተዋል።

አሁን ላይ የበርጊታ ዕድሜ በዘጠናዎቹ ውስጥ ነው። ጤናዋ እንደምትፈልገው ባለመሆኑ የሰው ድጋፍ ቢያስፈልጋትም ከሁሉ በላይ በፍቅር የሚንከባከባት ኃያል አምላክ እንዳላት በጽኑ ታምናለች። በዚህ ዕድሜዋ ኢትዮጵያ ውስጥ እየሆነ ያለውን በተቻላት

መጠን ትከታተላለች። አገራችንን እያንገዳገደ ያለው ክፍፍልና ጥላቻ የቤተክርስቲያን አባላትን ሊለያይ ይችላል የሚል ፍራቻ አላት።

ፍርሃቷን ማገድ የሚችለው በሷና በሮላንድ ውስጥ የነበረው የመድኃኒታችን የክርስቶስ መንፈስ በልባችን ውስጥ ጌታ ሲሆን ብቻ ነው።

ለሰዎች ሁሉ፣ በተለይም ለተጎዱት የሚያዝን ልብ ይስጠን። ዝው

ድርባ ፈቃዱ



**ለአገራችን ኢትዮጵያ እና ለቤተክርስቲያናችን**

**ታላቅ ባለውለታ ለነበረው**

**ዶ/ር ሮናልድ ኬዝን**

**በዘመኑ ወጣቶች የነበርን ለባለቤቱ በርጊታ ኬዝን እና ቤተሰቡ**

**ከፍ ያለ ምስጋናችንን እናቀርባለን**

# የትዳር ሥንክሣር

የትዳር ብክነት ወይም ውድቀት የሚወሰነው ገና ከጅምሩ ነው። ትዳር መመሥረት የሚያስቡ ሰዎች ከሁሉ ቅድሚያ ሊሰጡት የሚገባ ነገር ጉዳዩን ከተራ ውሳኔዎች በላይ መሆኑን በመገንዘብ በጥንቃቄና በጸሎት ለጉዳዩ ትኩረት መስጠት እንዳለባቸው ነው።

ሊያስቡበት ከሚገባቸው ነገሮች ዋናው ሊመሠርቱት የሚያቅዱት ትዳር እግዚአብሔር የሚከብርበት ነው ወይ? ብሎ ራስን መጠየቅ ሲሆን እንደ መመሪያ አድርጎ ሊከተሉት የሚገባ ጉዳይ ደግሞ መሠረቱ በተቀደሰ ዓላማ ላይ ብቻ የተመሠረተ እንዲሆን ነው።

ከትዳር ምሥረታው ቀጥሎ ባለትዳሮቹ ግንኙነታቸው ሁሉ እግዚአብሔር የሚከብርበት ለማድረግ የሚጠበቅባቸውን ሁሉ በጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው። ይህንን በተሳካ መንገድ ለማከናወን በየዓመቱ ግንኙነታቸውን በጋራ መገምገምና ማስተካከል ያለባቸውን ማወቅና መተግበር አስፈላጊ ነው።

በትዳር ውስጥ የልጆች በረከት እንዳለ ማወቅና ስለ ልጆቻቸው ማቀድ ያለባቸውን በቅድሚያ ማሰብና ማቀድ ተገቢ ነው። ልጆችን ያለዕቅድ ወደዚህ ዓለም አምጥቶ ለእነርሱም ሆነ ለሌሎች ሸክም እንዲሆኑ የማድረግ ኃላፊነት አልተሰጣቸውም። (Messages to Young people p. 462)

በዚሁ መጽሐፍ ላይ ስለልጆቻቸው የወደፊት ሕይወት ስለትምህርታቸውና ቀጥሎ ስለሚያስፈልጓቸው ነገሮች ሳያቅዱ መቅረት ማለት ልጆች ተገቢውን ጥንቃቄ ምግብና ልብስ እንዳያገኙ ማድረግ ስለሆነ ወንጀል ነው ይላል።

ሌላው በጣም አሳሳቢና መቀጨት ያለበት የትዳር ሕይወት ጋሬጣ በስሜታዊነት ሠንሰለት መተብተብ ነው። ባለንበት ክፉ ዓለም ስሜታዊነትን እንደመልካም ነገር የሚታይና ተገቢውን ትኩረት እያገኘ አይደለም።

ስሜታዊነት የሥጋን ፍትወታዊ ፍላጎት ለማርካት ሲባል ሊገታ በማይቻል ግፊት መሄድ ሲሆን ምክኒያታዊነትን ቁጥጥርን የማይቀበል አደገኛ አካሄድ ነው። ውጤቱም ስቃይና ሞት ነው።

በዚህ አደገኛ ባህሪ ብዙውን ጊዜ የጥቃት ሰለባዎች የሚሆኑት ሴቶች ናቸው። ጥቃት አድራሾችም በስሜታዊ ወጥመድ ውስጥ ያሉ የገዛ ባሎቻቸው ናቸው። እነዚህ በስም ባሎች ቢባሉም በባህሪያቸውና በአደራረጋቸው በትዳር ጓደኞቻቸው ላይ ጭካኔንና በሰብዓዊ ፍጡር ላይ ሊደረጉ የማይገባቸውን ድርጊቶችን የሚፈፅሙ ናቸው።

ስሜታቸውን ከማርካት አልፈው ስለ ሚስቶቻቸው የወደፊት ሕይወት ሊገጥሟቸው ስለሚችሉ የኑሮም ሆነ የጤና ችግሮች ደንታ የላቸውም። ከዚህ የተነሳ እናቶች የመከራ ሕይወት እንዲኖሩ ምክኒያት ይሆናሉ። በየዓመቱ ልጆችን በልጆች ላይ መውለድ ለልጆቻቸው የሚሰጡትን ምግብና የሚያለብሷቸውን ልብስ እንዲሁም ለጤናቸው የሚያስፈልጓቸውን ጥንቃቄዎች በማጣት መሰቃየት ወዘተ።



ዓለማችን ይህንንና ይህንን በሚመስሉ ስቃዮች ተሞልታለች፤ ስቃዩን የበለጠ መራራ የሚያደርገው ደግሞ የክርስቲያን ባለትዳሮች በዚህ የስሜታዊነት ሠንሠለት ተተብትበው ማየት ነው።

ከዚህ አደጋ ለመራቅ መሻትን መግዛት ወይም ራስን መቆጣጠር ትልቅ ቦታ ሊሰጠው ይገባል። በሮሜ 8፡13 ላይ እንዲህ የሚል ቃል አለ "እንደ ሥጋ ፈቃድ ብትኖሩ ትሞቱ ዘንድ አላችሁና በመንፈስ ግን የሰውነትን (የሥጋን) ሥራ ብትገድሉ በሕይወት ትኖራላችሁ"።

መሻትን መግዛት የእግዚአብሔር ስጦታ እንጅ በራሳችን ኃይል የምንፈፅመው አይደለም። ታዲያ ምን ያስፈራናል? በዮሐ 3፡34 ላይ ደግሞ "… እግዚአብሔር መንፈሱን ሰፍሮ አይሰጥምና…" ይላል። ይህ ማለት የሥጋን ፍላጎትና ስሜታዊነትን የምናሸንፍበትን መንፈስ እግዚአብሔር ይሰጠናል። ሲሰጥም አትረፍርፎ ነው። በመንፈሱም የማናሸንፈው ኃጢያት የለም። ምንም ጊዜ ሳናባክን አሁን ይህን እንዲሰጠን እንለምን። ከልብ የነገሩትን የሚሰማ የለመኑትን የሚሰጥ አምላክ መንፈሱን አትረፍርፎ ይሰጠናል። ስሜታዊነታችንንም አሸንፈን ለትዳር ጓደኞችንና ለልጆቻችን በረከት እንሆናለን።

**ፓስተር ከገኘሁ ወንድም**

# የቀደመው እባብ ዲያብሎስ፡ ሰይጣን

በገነት ውስጥ ብዙ ዓይነት እንስሶች ነበሩ። ከአራዊት ሁሉ ግን አንድ የተለየ ፍጡር ነበር። "እባብ እግዚአብሔር አምላክ ከፈጠራቸው የዱር አራዊት ሁሉ ተንኰለኛ ነበረ" (ዘፍጥረት 3:1)።

የዘፍጥረት መጽሐፍ በተጻፈበት የዕብራይስጥ ቋንቋ "ተንኮለኛ" ተብሎ የተተረጎመው ቃል "ዓሩም" የሚል ሲሆን፤ "ብልጥ"፣ እንዲሁም "ጠቢብ"፣ ወይም "አዋቂ" በሚሉት ቃላትም ሊተረጎም ይችላል።

ኃጢአት ባልነበረበት ዓለም ውስጥ ከክፋት የጸዳ ጥበብ እንደነበረ ማወቁ ወሳኝ ነው። በተጨማሪ ያ ጥበብ በርኩሰት ሲጠለሽ፤ ወደ ተንኮል ሊለወጥ እንደሚችል መረዳት ዛሬ ለምንኖርባት ዓለም እንቆቅልሽ የሆኑ መሠረታዊ ችግሮች መንስኤው ምን እንደሆነ ስለሚገልጥ ነው።

በአይሁድ አስተሳሰብ ጥበብና ውበት የተቆራኙ ናቸው። ጠቢቡ ሰሎሞን ይህንን ሲገልጥ እንዲህ ይላል፣ "ጥበብን አግኛት፤ ... በራስህ ላይ ሞገሳማ አክሊል ትደፋልሃለች" (ምሳሌ 4:7፣9)።



የጥበብና የውበት ሁሉ ምንጭ የሰማይ አምላክ ነው። ስለሆነም ሁሉን መልካም አድርጎ ሲፈጥር እባብንም ከአራዊት ሁሉ ውብና ብልህ አድርጎ ሠርቶ ነበር ማለት ነው።

ዘፍጥረት ምዕራፍ 3 ላይ ያለውን ውብና ብልህ እባብ ቀረብ ብለን ስንመረምር ተራ እባብ አለመሆኑን እንረዳለን። ሔዋንን የቀረበበት መንገድ ክፋትና ብልጠት የተሞላበት ስለነበር እባብ የተገለጸበት ቃል "ተንኮለኛ" የሚል ትርጉም ቢሰጠው አይገርምም። ሆኖም ይህ ውብ እንስሳ ክፋት ባልነበረበት ገነት ውስጥ ተንኮልን እንዴት ተማረ? ብለን እንድንጠይቅ ይጋብዛል። በመቀጠል ይህ እባብ ከሔዋን ጋር በሰው ልሳን ሲነጋገር ይታያል። እንስሳት የሰው ንግግር ሰምተው ሲታዘዙ ማየት ያስገርማል፤ ምን ያህል ብልሃት እንዳላቸው ያሳያል። አፋቸውን ከፍተው ሲናገሩ መስማት ግን ያስደነግጣል።

"ሴቲቱንም፣ 'በእርግጥ እግዚአብሔር ፣ "በአትክልቱ ስፍራ ካሉ ዛፎች ከማናቸውም እንዳትበሉ" ብሎአልን?' አላት" (ዘፍጥረት 3:1)።

ንግግር የሃሳብ መግለጫ ነው። ከምንሰማቸው ቃላት በስተጀርባ መሪ ልብ ተሰውሯል። ይህን ካወቅን እባብ ሔዋንን የጠየቃት ጥያቄ እባብን ወይም አራዊትን የማይመለከት ጉዳይ መሆኑ እጅግ ይገርማል። በገነት ስላለው ጤናማ አየር ወይም ስለ ገነት የመልከዓ ምድር ምቾት ቢያወራ መደነቃችን ይቀንስ ነበር። ከማውራቱ ባሻገር ግን ስለ እግዚአብሔር አስተዳደር ጥያቄ ማንሳቱ ከጥያቄው በስተጀርባ የማን ልብ እንዳለ ይጠቁማል።

ከላይ በዘፍጥረት 3፡1 የተጠቀሰው የእባቡ ጥያቄ ጥርጣሬ የሚያጭርና ቶሎ ለመመለስ የሚያጓጓ ነው። ለሔዋን አዛኝ በመምሰል ፈጣሪ ደስታ ከልካይ መሆኑን ማሰብ እንድትጀምር መራት። ሔዋን የእግዚአብሔር ስም እንዳይጎድፍ በምታደርገው የመከላከል ርብርብ የተሸናፊነት ስነልቦና ውስጥ ገባች።

እባቡ እውነትም ተንኮለኛ ነበር፤ ተንኮሉ ግን ተራ የእንስሳ ተንኮል አልነበረም። ሔዋንን በጥርጣሬ ሸብቦ ወደ ክህደት የሚያስገባ ተንኮል መሆኑን ስናይ ከሰው ብልሃትም ያለፈ ረቂቅ ነገር እንዳለበት ያስታውቃል።

"ሴቲቱም እባቡን እንዲህ አለችው፤ 'በአትክልቱ ስፍራ ካሉት ዛፎች ፍሬ መብላት እንችላለን፤ ነገር ግን እግዚአብሔር 'በአትክልቱ ሥፍራ መካከል ከሚገኘው ዛፍ ፍሬ እንዳትበሉ፤ እንዳትነኩትም፤ አለበለዚያ ትሞታላችሁ' ብሏል'" (ዘፍጥረት 3:2-3)።

እባብ ጥያቄውን ያነሳው ካለማወቅ ወይም ከየዋህነት የተነሳ ቢሆን የሔዋን መልስ አጥጋቢ ይሆንለት ነበር።

እባቡ ግን እጅግ ተንኮለኛ ነበር፤ ድብቅ ዓላማ ነበረው። መከፈቻው ላይ ያነሳው ጥያቄ ለእኩይ ፍላጎቱ መሸጋገሪያ ነበር።

“እባቡም ሴቲቱን እንዲህ አላት፤ ‘መሞት እንኳ አትሞቱም፤ ከፍሬው በበላችሁ ጊዜ ዐይናችሁ እንደሚከፈትና መልካምና ክፉን በማወቅ፣ እንደ እግዚአብሔር እንደምትሆኑ እግዚአብሔር ስለሚያውቅ ነው’” (ዘፍጥረት 3:4-5)።

እባብ ሞትን በለስላሳ አንደበቱና ማራኪ ውበቱ ደብቆ ነው ሔዋንን የቀረበው። አምላክ ላይ ስለማመጽና የኃጢአት መጨረሻ ስለሆነው ሞት በእውነት ማውራት ቢጀምር ሔዋንን ሊያስደንግጣት ይችል ነበር። ስለሆነም ጥያቄውን የዋህ መልክ አስይዞ ሔዋን ራሷ ስለ አመጽና ሞት ግኑኝነት እንድታነሳ መንገድ ከፈተላት።

ቀጥሎም እግዚአብሔርን አለመታዘዝና ሞት ግኑኝነት እንደሌላቸው ተናገረ። “መሞት እንኳ አትሞቱም” በማለት ሞትን ካቀለለ በኋላ፤ ከህደት ሰውን ረቂቅ የሆነ እውቀት አላብሶ ወደ አምላክነት ከፍ እንደሚያደርግ ተናገረ። በሔዋን ላይ ስነልቦናዊ የበላይነት እንደያዘ ግልፅ የሚሆነው የንግግሩ ውጤት ሲታይ ነው። ሞትን እንደ ቀልድ ንቆ ሔዋንን ወደ እግዚአብሔር ከፍታ በቀላሉ የማድረስ ዕውቀት የያዘ መስሎ ሲቀርብ የሔዋንን የማወቅ ጉጉት ገዛ።

“ሴቲቱ የዛፉ ፍሬ ለመብል መልካም፣ ለዐይን የሚያስደስትና ጥበብንም ለማግኘት የሚያጓጓ እንደሆነ ባየች ጊዜ፣ ከፍሬው ወስዳ በላች፤ ከእርሷም ጋር ለነበረው ለባሏ ሰጠችው፤ እርሱም በላ” (ዘፍጥረት 3:6)።

እንዲህ ዓይነቱ የማሳመን ችሎታ እውን ከእንስሳ የፈለቀ ነው? ለመሆኑ ይህ ሔዋንን ያሳሳተው ተንኮለኛ እባብ ማን ነው? የእንስሳ መልክ ይዞ ከሔዋን ጋር ያወራው ማን ነው?

ባለ ራዕዩ ዮሐንስ በሰማይ ጦርነት ከተደረገ በኋላ አንድ እባብ ወደ ምድር መጣሉን ይናገራል።

“ታላቁ ዘንዶ፣ የጥንቱ እባብ ተጣለ፤ እርሱም ዲያብሎስ ወይም ሰይጣን ተብሎ የሚጠራው፣ ዓለምን ሁሉ የሚያስተው ነው፤ እርሱ ወደ ምድር ተጣለ፤ መላእክቱም ከእርሱ ጋር ተጣሉ” (ራዕይ 12:9)።

ሔዋን በየዋህነቷ ለዘላለም እንዳትኖር በተንኮሉ የጠለፋት ሰይጣን ነው። ይህ እባብ ጥንት በኃጢአት ከመውደቁ በፊት ከመላዕክት ሁሉ በላይ ውብና አዋቂ የነበረው የብርሃን ፍጡር ነው። ራሱን እጅግ በመውደዱና ለመመለክ ስለፈለገ፤ አብረውት የነበሩትን መላዕክት ለማሳሳት ሲል ፈጣሪ የሰጠውን ጥበብና ውበት ተጠቅሞ ለመጀመሪያ ጊዜ ውሸትና ተንኮልን ፈጠረ። ሆኖም ቀድሞ እውቀትና ውበትን የተሞላ ስለነበር ተንኮለኛ ባህሪውን ለማጋለጥ እጅግ ከባድ ነበር።

ሔዋንን ለማሳሳት ዲያብሎስ በገነት ካሉት እንስሳት ሁሉ እባብን መጠቀሙ አይገርምም። የገነቱ እባብ እንደዛሬ በምድር እየተሳበ፣ ሰዎችንና እንስሳትን አስደንግጦ የሚናደፍ አልነበረም። ዲያብሎስ ከመውደቁ በፊት ከመላዕክት ሁሉ በውበትና በጥበብ ይልቅ እንደነበረው፤ እባብም ከእንስሳት ሁሉ ውብና ብልህ ፍጡር ነበር። ሰይጣን ለውስብስብ ተንኮሉ ተራ እንስሳ መጠቀም ዓላማውን ሊያጋልጥ እንደሚችል ስለገመተ፤ በሚያምርና በገነት ውስጥ በብልሃቱ እውቅና በነበረው እባብ ተመስሎ ለመቅረብ ወሰነ።



ዲያብሎስ እባብን አሳምኖ ወይም አስገድዶ አልተጠቀመበትም። አምላክ የፈጠረው ሁሉ መልካም እንደነበር ቃሉ ይናገራል፤ “እግዚአብሔርም ያደረገውን ሁሉ አየ፤ እነሆም፣ እጅግ መልካም ነበረ” (ዘፍጥረት 1:31)። መልካም የነበረው ተፈጥሮ በገነት የነበሩትን

እንስሳት ያጠቃልላል። ስለሆነም እንስሳት ከሰይጣን አምባገነናዊ ቁጥጥር ውጭ ነበሩ። ታዲያ ዲያብሎስ እንዴት በእባብ ተጠቅሞ ሔዋንን አሳሳታት?

ሰይጣን ራሱ ወደ እባብ ለውጦ ወይም ተመስሎ ነው ሔዋንን ያነጋገራት። ሰይጣን ተለዋዋጭ ውጫዊ ባህሪዎችን በመላበስ የማሳሳት ዓላማውን ዛሬም እንደሚያሳካ ቃሉ ሲናገር እንዲህ ይላል፤

“ነገር ግን እባብ ሔዋንን በተንኰል እንዳሳታት ምናልባት የእናንተም ልቡና ተበላሽቶ ለክርስቶስ ካላችሁ ቅንነትና ንጽሕና እንዳትወሰዱ እሠጋለሁ … ይህም የሚያስደንቅ ነገር አይደለም፤ ምክንያቱም ሰይጣን ራሱ የብርሃን መልአክ ለመምሰል ራሱን ይለዋውጣል” (2 ቆሮንቶስ 11:3፣14)።

ዲያብሎስ እግዚአብሔርን ይጠላል። ጥላቻውን በግልፅ ቢያሳይ ግን ብዙ ተቀባይነት እንደማያገኝ ጠንቅቆ ያውቃል። ስለሆነም ሰዎችን ለመተናኮል ዘመድ ወይም አዛኝ ወዳጅ መስሎ መቅረቡን ይመርጣል። ላለፉት ስድስት ሺህ ዓመታት በዚህ ስልት የሰውን ዘር እያሳሳተ ወደ ሞት ገደል አስገብቷል።



ሰይጣን እንደ እስስት ይለዋወጣል። ለሔዋን በተናገረበት ጣፋጭ አንደበት ዛሬም የሚሰሙትን ያሳስታል። በገሃድ ሰይጣን ሆኖ ቢገለጥና፣ ሰዎችን ለርኩሰት ቢያነሳሳ በድንጋጤ እንደሚሸሹት ያውቃል። ከህደትና አመጽ ከፉ መሆናቸውን ብዙዎች በልምድና በምርምር ደርሰውበታል። ስለሆነም ዲያብሎስ መልኩን ለተቀባይ አሳምሮ መቅረቡን ተክኖታል።

ሰይጣን በመጠጥ ቤቶች ሁካታና በጦርነት እልቂት ውስጥ መንገሱ አይደንቅም። በፈላስፎች፣ በሳይንስ ምሁራንና በፖለቲካ መድረኮች ላይ ከፍ ማለቱ ብዙ አይገርም ይሆናል። በምንኖርበት ዘመን ግን ሰይጣን የክርስትና ልብስ ለብሶ፣ ቃለ እግዚአብሔርን በርዕቱ አንደበቱ እየጠቀሰ መስበክ እንደሚችል ብዙዎች አያውቁም። ባለማወቃቸውም ምክንያት ቤተክርስቲያን ውስጥ ብዙዎች በየዋህነት የእባቡን ምክሮች አጣጥመው እየዋጡ ነው።

ጥንት ጳውሎስ ይህንን ፈርቶ የቆሮንቶስን ሰዎች አስጠንቅቆ ነበር። “እንደነዚህ ያሉ ሰዎች የክርስቶስን ሐዋርያት ለመምሰል ራሳቸውን የሚለዋውጡ፣ ሐሰተኞች ሐዋርያትና አታላዮች ሠራተኞች ናቸው” (2 ቆሮንቶስ 11:13-14)።

በመጨረሻው ዘመን ሐሰተኛ ሐዋርያት እንደሚመጡ መጽሐፍ ቅዱስ አስቀድሞ ተንብይዋል። በምንኖርበት ዘመን ይህ ትንቢት አገራችን ውስጥ ሲፈጸም እያየን ስለሆነ ለማመን አይከብድም። የብልፅግናን ወንጌል የሚሰብኩ ሐዋርያት የኢትዮጵያን ቀልብ ገዝተዋል። እውነቱ ግን የክርስቶስን ምድራዊ ድህነትና ስቃይ በመካድ፤ ዓለማዊ ምቾት የጽድቅ ማሳያ መሆኑን የሚሰብኩ ሁሉ የጥንቱ እባብ ሐዋርያት መሆናቸው ነው። እግዚአብሔር ከፈተናና ከሕመም ነጻ የሆነ ምድራዊ ሕይወት እንድንኖር ስላዘዘ በስሙ በሽታን ሁሉ እንፈውሳለን የሚሉ መሃይም ሰባኪዎች፤ ታመውና ታርደው በሞቱት ነቢያትና የዕምነት ሰማዕታት ላይ የሚያላግጡ የዲያብሎስ ልጆች መሆናቸውን ሰዎች ቢያውቁ ከብዙ ሐዘን ይተርፉ ነበር።

ሔዋንን ያደናገራት ድንቅ ነገር ተናጋሪ እባብ ማግኘቷ ነው። አእምሮዋ ድንቁን ነገር ሲያሰላስል እባብ እንደ አምላክ መሆን ትችያለሽ የሚለውን ሃሳብ አቀረበላት። እባብ መናገር ከቻለ እሷ እንደ እግዚአብሔር የማትሆንበት ምን ምክንያት አለ ብላ ይሆን?

ካሉበት ተራ ሕይወት እጅግ ወደላቀ የጥቅም ከፍታ የመሻገር መብት እንዳላቸው ሲነገራቸው ለማመን የሚቸኩሉ ብዙ ክርስቲያኖች አሉ። ይህንን ውሸት የሚሰብከው ሰው ደግሞ እንደ እባቡ ድንቅ አድራጊ ሲሆን የበለጠ ፈታኝ ነው።

ሔዋን ስትፈተን ከኃጢአት የፀዳ መልካም ዓለም ውስጥ ትኖር ነበር። አምላክ ውብ አድርጎ በፈጠራት

ምድር ላይ ንግሥት ነበረች። ያጣችውና የጎደለባት ነገር አልነበረም። ሆኖም ምናባዊ የሆነ ጥቅም ለማግኘት ስትል የነበራትን ክብር አጣች። ዓለማችንም የአበሳ ገደል ውስጥ ተቀርቅራ እኛ የመከራው ገፈት ቀማሾች ሆነናል።

ኃጢአት ሰውን አወናብዶ ያዋረደና ዕድሜ ያሳጠረ ክፉ ነገር ነው። በአመጽ የተወጠረው የሰው ልብ ይህንን ውርደት መቀበል ይሳነዋል። ለማምለጥ ሲል አሁንም ወደ አምላክ ከፍታ ለመድረስ ባገኘው ዕድል ሁሉ ይንጠራራል። ንስሐንና ለእግዚአብሔር ሕግጋት መገዛትን እንደ ሽንፈት የሚቆጥረው የሰው ልብ፤ በዘመናት ሁሉ ከፈጣሪው ፈቃድ ጋር ሲዋጋ ቆይቷል። ታዲያ የዚህ ውዝግብ መጨረሻ ምንድነው?



ባለ ራዕዩ ዮሐንስ በዘመን መጨረሻ ስለሚሆነው ሲተነብይ እንዲህ ይላል፣ “ዓለም በሙሉ በመደነቅ አውሬውን ተከተለው። ሰዎችም ለዘንዶው ሰገዱለት” (ራዕይ 13:3-4)።

ሰዎች ለዘንዶው የሚሰግዱለት በዘንዶነቱ ሳይሆን የብርሃን መልአክ በመምሰሉ ነው። የሰዎች ልብ ውስጥ እያደገ ያለው የአመጽ መንፈስ ለሰይጣን ወለል ብሎ የተከፈተ በር ነው። በተጨማሪ ዲያብሎስ ለስድስት ሺህ ዓመታት ሰዎችን በማታለል ያካበተው ልምድ አለ። ይህ የመጨረሻው ዘመን ፈተና ሔዋን ከገጠማት ውሸት የረቀቀ መሆኑን ይጠቁማል።

ሔዋን የተፈተነችው እግዚአብሔርን እንዳታምነው ነው። ክህደቷን ለማሳየት ደግሞ ትዕዛዙን ተላለፈች። ይህ የማይቀየር የዲያብሎስ አሠራር መሆኑ ዛሬም ይታያል። ሰዎች ክህደታቸውን ሕግጋቱን በመጣስ እንዲገልጡ ሰይጣን ቤተክርስቲያን ውስጥ ሆኖ በዘመኑ “ወንጌላውያን” እየሰበከ ነው። ብዙ ቤተ አምልኮዎች በድንቅ፣ በተዓምራትና በሚጥሙ መዝሙሮች የታጀቡ የክህደት ገደሎች ሆነዋል። የአምላክን ትእዛዛት መታዘዝ እንደማያስፈልግና፤ ፀጋው በሚሰጠው “ነፃነት” ከርኩሰት ጋር መኖር ነውር እንደሌለው ብዙዎች የሚያምኑት ስለተሰበከላቸው ነው።

ሔዋን ባለመታዘዝ አልተጠቀመችም። ዛሬም አለመታዘዝ ምንም ጥቅም የለውም። ይልቁንም በዘመኑ መጨረሻ ለሚመጣው ታላቅ ፈተና ተጋላጭ ያደርገናል። ቃሉም ይህንኑ ይላል፤ “ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ በታረደው በግ የሕይወት መጽሐፍ ላይ ስሞቻቸው ያልተጻፈ የምድር ሰዎች ሁሉ ለአውሬው ይሰግዳሉ” (ራዕይ 13:8)።

በታረደው በግ የሕይወት መጽሐፍ ስሞቻቸው የተጻፉላቸው እነማን ናቸው? መጽሐፍ ቅዱስ መልሱን ሲሰጥ ይህንን ይላል፤ “የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የሚጠብቁና ለኢየሱስም ታማኝ ሆነው በትዕግሥት የሚጸኑ ቅዱሳን” ናቸው (ራዕይ 14:12)።

የእግዚአብሔርን ሕግጋት ማንም ሊያሻሽል ወይም ሊሽር አይችልም። ትእዛዛቱ የሕይወት መሠረት ናቸው። ሰይጣን የአምላክ ትዕዛዛት ተሽረዋል ብሎ ሕዝበ ክርስቲያንን ቢያታልልም፤ ሰው ከአመጽ መንፈስ ሳይላቀቅ ከነርኩሰቱ ሰማይ አይገባም። አሳሳቹ እባብ በብልጠት እያታለለ ሊበልጠን ቢሞክርም ቃሉ የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው እንደሚል በፈሪኻ እግዚአብሔር በምናገኘው ጥበብ ብልጠቱን ልናከሽፍ እንችላለን (ምሳሌ 9፡10)።

ስለዚህ ከሔዋን ስህተት ተምረን ቃለ እግዚአብሔርን ሳናወላውል መታዘዝ ግድ ይላል። ምድራዊ ምቾትና ተዓምራትን መሠረት ያደረገ “ክርስትና” የእባቡ ወንጌል ነው። ሰዎች ከምድር ስቃይና ከሞት ማምለጥ የሚችሉት የእግዚአብሔርን ቃል ጠንቅቆ በመመርመርና በመታዘዝ ብቻ ነው (ሮሜ 2፡13)። የምንድንበት ሌላ ምቹ አቋራጭ የለም (የሐዋርያት ሥራ 4፡12)። መስቀላችንን በትህትናና በንስሐ ተሸክመን ከአሳሳች ወንጌሎች ሁሉ መራቅ አለብን።

በዚህ የመጨረሻ ዘመን የእባቡን ስህተቶች ለመቃወም ማስተዋል ከሚያገኙ ጠቢባን መካከል ያድርገን።

“ብዙዎች ይነጻሉ፤ ይጠራሉ፤ እንከን አልባም ይሆናሉ፤ ክፉዎች ግን በክፋታቸው ይጸናሉ፤ ከክፉዎች አንዳቸውም አያስተውሉም፤ ጠቢባን ግን ያስተውላሉ” (ዳንኤል 12:10)።

**ደርባ ፈቃዱ**

# አሜሪካ በእርግጥ በትንቢት የተጠቀሰች አገር ናት?

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ቀደምት መንግሥታትና አነሳስ ብዙ የተናገረው አለ። ስለ ባቢሎን፣ ሜዶና ፋርስ፣ ግሪክ፣ ሮምና የተከፋፈሉት የአውሮጳ መንግሥታት በዳንኤል 2 በትንቢት ተነግሮ እናገኛለን። የእነዚህ መንግሥታት አነሳስ ብቻ ሳይሆን አወዳደቃቸውና በቀጣዩ መንግሥት ሲተኩ ያለውን ሒደት መጽሐፍ ቅዱስ በቂ ትንተና ይሰጣል።

አሁን ባለንበት ዘመን ስላሉት መንግሥታት መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል ብለን ብንጠይቅ ብዙ መልሶች ሊሰጡ ይችላሉ። በተለያዩ የሚዲያ መድረኮችና የስብከት ቦታዎች ስለ ዘመናችን የትንቢት አፈታትና የመንግሥታት ሁኔታ ትንቢታዊ ከሚባሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እየተጠቀሰ ሲተነተን ሰምተን ሊሆን ይችላል።

ከዚህ ሁሉ ግን በጣም የሚያስደንቅ በሚባል መልኩ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ አሜሪካ አነሳስና የመንግሥታዊ አሠራር እንዲሁም የወደፊት ዕጣ ፈንታ በትንቢት ተናግሯል። አሜሪካ ለምን ተመሠረተች? በዓለም የመጨረሻ ታሪክ ውስጥ ያላት ሚና ምንድነው? የምድራችን ኃያል አገር ሆና በሃይማኖቱ መስመር የምትጫወተውስ ምንድነው? አሜሪካ ወደፊት መልኳን ትቀይር ይሆን? ነጻነትን




የተላበሰው መንግሥታዊ አሠራሯ ይለወጥ ይሆን? ወዘተ የሚሉትንና ሌሎች ጥያቄዎች በስፋት በዚህ ትምህርት እንዳስሳለን። ለዚህ ትምህርት ይረዳ

ዘንድ ራዕይ ምዕራፍ 13፡11-18 ያሉት ጥቅሶች በቅድሚያ ሊነበቡ ይገባል።

1. **በራዕይ 13 ሁለት የዓለም ኀይላት ተጠቅሰዋል፤የመጀመሪያው ማነው?**

ከዚህ በፊት እንዳጠናነው በራዕይ 13፡1-10 የተጠቀሰውና ሰባት ራሶች ያሉት አውሬ የሮም ጳጳሳዊ ኃይል ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘ “አውሬ” የሚለውን ቃል መጽሐፍ ቅዱስ ሲፈታው የዓለም መንግሥት ወይም ኃይል ነው ይለዋል። “እነዚህ አራቱ ታላላቅ አራዊት ከምድር የሚነሡ አራት ነገሥታት ናቸው” እና “አራተኛይቱ አውሬ በምድር ላይ አራተኛ መንግሥት ትሆናለች” ዳን 7፡17፣23።

2. **የሮም ጳጳሳዊ ሥርዓት መቼ (በስንት ዓም) ነበር ያከትማል የተባለው?**

“በአርባ ሁለት (42) ወርም እንዲሠራ ሥልጣን ተሰጠው” (ራዕይ 13፡5)።

በዓለም በተለይም በአውሮጳ ለዘመናት በሥልጣን መንበር ላይ የነበረው የሮም ጳጳሳዊ ኃይል ልክ መጽሐፍ ቅዱስ እንደተነበየው ጊዜው ሲደርስ ከመንበሩ ተነስቷል። ከዚህ በፊት ስለ ትንቢታዊ ቀናት ስናጠና እንደተማርነው የቀን-ለዓመት ስሌትን በመከተል አንድ የትንቢት ቀንን ወደ ዓመት

በመቀየር ሒሳባዊ ቀመሩ እንዴት ከታሪክ ጋር በተሰናሰለ ሁኔታ ትንቢት ሲፈጸም እንደኖረ አጥንተናል። በዚህ መሠረት 42 የትንቢት ወራት ማለት 1,260 ቀናት ወይም የትንቢት ዓመታት መሆኑን እንረዳለን (ሕዝ 4፡6፤ ዘኍልቍ 14፡34)።

አንድ ዓመት 12 ወራት አሉት፤ በ3 ዓመታት ደግሞ 36 ወራት (3x12 = 36) አሉ። በትንቢቱ ከተሰጠው 42 ወራት 36 ስንቀንስ 6 ወራት ይቀሩናል። ስለዚህ 42 ወራት ማለት 3 ዓመት 1/2 ወይም 1260 የትንቢት ቀናት መሆኑን እንረዳለን። ይህም ጳጳሳዊ ሥርዓት በሥልጣን የቆየበት ዘመን ነው። ይህ ሥልጣን ደግሞ በወቅቱ የፈረንሣይ ንጉሥ የናፖሊዮን ጄኔራል የነበረው በርቲየር እኤአ በ1798ዓም በዚያን ጊዜ የነበሩትን ጳጳስ (ፖፕ) ከመንበራቸው ባወረደበት ጊዜ ትንቢት ተፈጸመ፤ አውሬውም ለሞት በሚያደርስ ቁስል ቆሰለ!

### 3. ጳጳሣዊ ሥርዓት ለሞት በሚያደርስ ቁስል ሲቆስል የትኛው መንግሥት ወደ ሥልጣን መጣ?



“ሌላም አውሬ ከምድር ሲወጣ አየሁ፥ የበግ ቀንዶችን የሚመስሉ ሁለት ቀንዶችም ነበሩት እንደ ዘንዶም ይናገር ነበር” (ራዕይ 13፡11)።

በራዕይ 13፡10 እንደተጠቀሰው ጳጳሣዊ ሥርዓት ለሞት በሚያደርስ ቁስል የቆሰለው በ1798 ዓም ነበር። ልክ በዚያው ዘመን አካባቢ ነበር (ቁጥር 11) አሜሪካ እንደ አገር ብቅ ማለት የጀመረችው። በ1776 ዓም አሜሪካ ነጻነቷን አወጀች፤ ሕገመንግሥቱ በ1787 ጸደቀ፤ የሙብት ማስጠበቂያ ድንጋጌ (Bill of Rights) በ1791 ዓም በሥራ ላይ ዋለ፤ በ1798 አሜሪካ በገሃድና ሁሉ በሚያውቀው መንገድ የዓለም ኃያል የምትሆንበትም ፈር እየቀደደች መጣች። እነዚህና ከትንቢት ቃላት ጋር ስናነጻጽራቸው ይህንን ሁሉ መሥፈርት የምታሟላው ከአሜሪካ በስተቀር ማንም ሊሆን አይችልም።

### 4. “ከምድር ሲወጣ” የታየውን አውሬ ልዩ የሚያደርገው ምንድነው?

“ሌላም አውሬ ከምድር ሲወጣ አየሁ” ራዕይ 13፡11።

በዳንኤልና ራዕይ መጻሕፍት መንግሥታትን የሚወክሉት አራዊት ባብዛኛው ሲወጡ የሚታዩት ከባሕር ነው። አንድ አውሬ ወይም መንግሥት ከባሕር መውጣቱ የሚያመለክተው በርካታ ሕዝብ ካለበት ቦታ የሚነሳ መሆኑ ነው። “አለኝም፡- ጋለሞታይቱ የተቀመጠችባቸው ያየሃቸው ውኃዎች፥ ወገኖችና ብዙ ሰዎች አሕዛብም ቋንቋዎችም ናቸው” (ራዕይ 17፡15)። ጥቅሱ እንደሚያመለክተው ውኃዎች የተባሉት ባሕር ወይም ብዙ ውሃ ያለበትን ሲሆን ይህም “ወገኖችና ብዙ ሰዎች አሕዛብም ቋንቋዎችም” የሚሳይ ነው። ምድር ደግሞ የብዙ ውኃዎች ተቃራኒ ስለሆነ ይህ ከምድር ወጣ የተባለው መንግሥት የሚነሳው ብዙ ሰው ከሌለበት ቦታ ነው በሚለው ልንወስደው እንችላለን። ከዚህ አንጻር ከተመለከትነው አሜሪካ በምትነሳበት ወቅት “አዲሱ አገር” ወይም “New World” የሚባለው አሁን አሜሪካ ያለችበት ቦታ ሕዝብ ያልሰፈረበት ባዶ የሚባል ቦታ ነበር።

### 5. በበግ የተመሰለው አውሬ ላይ ያሉት ቀንዶች የሚያመለክቱት ምንድነው? ዘውድ የሌለውስ ለምንድነው?

“አሥሩም ቀንዶች ከዚያ መንግሥት የሚነሡ አሥር ነገሥታት ናቸው” (ዳንኤል 7፡24)፤ “በዓይኖቹም መካከል ያለው ታላቁ ቀንድ መጀመሪያው ንጉሥ ነው” (ዳንኤል 8፡21)።

ቀንድ የሚያመለክተው መንግሥታትን ወይም ነገሥታትን ነው። አሜሪካ ንጉሥ አልባ አገር ነች፤ ነገርግን አሜሪካንን የሚገዛት ንጉሥ ሳይሆን ሁለት መሠረታዊ መመሪያዎች ናቸው። እነዚህም የሲቪልና የሃይማኖት ነጻነት ናቸው። እነዚህ መመሪያዎችም አንደኛው “ሪፓብሊካዊነት” (ንጉሥ አልባ መንግሥት ወይም “ሪፑብሊክ” ማለት ሕዝብ በሚመርጣቸው ተወካዮች ወይም እንደራሴዎች የሚመራ መንግሥት ማለት ነው)፤ ሁለተኛው

ደግሞ “ፕሮቴስታንትነት” (ጳጳስ የማይመራው ቤ/ክን) ነው።




ከጥንት ዘመን ጀምሮ ሃይማኖትና መንግሥት የተሳሰሩ ሆነው ኖረዋል። የመንግሥት ሃይማኖት የሚባል ከመንግሥት ጋር በትሥሥር የሚሠራ ሃይማኖት ሲኖር የሃይማኖቱ መሪዎች ነገሥታትን በመሾምና በመቀባት የላቀውን ሚና ሲጫወቱ ኖረዋል። መንግሥታትም በበኩላቸው የሃይማኖት ድርጅቱን ለመደገም በሕዝብ ላይ ግብር ሲጭኑና ሲጨቁኑ እንደነበር ታሪክ ያስታውሳል።

አሜሪካ ከዚህ የተለየች ነች። እንደ ቀደምት መንግሥታት ሳይሆን አዲስ ሥርዓትን ነው የጀመረችው። ማንኛውም ሰው የፈለገውን እንዲያመልክ ወይም የፈለገውን ሃይማኖት እንዲከተል ነጻ የምትሰጥ አገር ብቻ ሳትሆን መንግሥት በሃይማኖት ውስጥ ጣልቃ እንደማገባ በግልጽ በሕግ የደነገገች አገር ናት።

ስለዚህ በአውሬው ላይ ዘውድ አለመኖሩ የሚያመለክተው በሕዝብ የሚመረጥ መሪ እንጂ በንጉሥ የሚተዳደር መንግሥት እንዳልሆነ ነው። “የበግ ቀንዶችን የሚመስሉ ሁለት ቀንዶች” የሚያሳዩት ይህች አገር ሰላም ወዳድ፣ ነጻነት የሞላባት፣ ጭቆና የማትቀበል፤ መልካም አገር መሆኗን ነው። ጥያቄው ያለው በዚሁ ትቀጥላለች ወይ የሚለው ነው፤ መልሱን ጥናታችንን ስንቀጥል እናገኘዋለን።

## 6. በራይዕ 13፡11 ላይ ለምንድነው በጉ እንደ ዘንዶ ይናገራል የሚለው?

“… እንደ ዘንዶም ይናገር ነበር” (ራዕይ 13፡11)።

ከዚህ በፊት እንደተማርነው ዘንዶው ሰይጣን ነው፤ ሰይጣን ደግሞ ዓላማውን የሚያሳካው በምድር በሚነሱ መንግሥታት አማካኝነት ነው። የራሱን መንግሥት በምድር ለመመሥረት የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማጥፋት ይጥራል፤ ይሠራል፤ የጌታን ተከታዮች ያሳድዳል፣ ይገድላል።

ስለዚህ በጉ እንደ ዘንዶ መናገሩ የሚያመለ ክተው በሰይጣን ቁጥጥር ሥር ሆኖ የሚሠራ መሆኑን ነው። አሜሪካ እንደ አጀማመሯ ነጻነትን በመስጠትና የሃይማኖትን እኩልነት በማስፈን የምትቀጥል ሳትሆን በመጨረሻው ዘመን ሰዎች የማይፈልጉትን እንዲያመልኩ የምታስገድድ፤ እምቢ የሚሉትን ደግሞ የምትቀጣ አገር ትሆናለች።

## 7. ይህ ለማመን የሚከብድ ጉዳይ ነው፤ ለመሆኑ አሜሪካ እንደ ዘንዶ ስትናገር የሚከሰቱት ነገሮች ምንድናቸው?

ከዚህ በታች አራት ወሳኝ ነጥቦች ተጠቅሰዋል፤

- “በፊተኛውም አውሬ ሥልጣን በእርሱ ፊት ሁሉን ያደርጋል” (ራዕይ 13፡12)። በዚሁ የራዕይ መጽሐፍ 13ኛው ምዕራፍ መጀመሪያ ላይ የተጠቀሰው ከባህር የወጣው አውሬ የሮም ጳጳሳዊ ሥርዓት ነበር፤ ይህ ኃይል በመካከለኛው ዘመን በርካታ ክርስቲያኖችን ያሳደደና የገደለ እንደነበር ታሪክ መስክሯል፤ ልክ እንደዚህ አሳዳጅ ኃይል አሜሪካም እንዲሁ ሰዎችን ወደ አስገዳጅ ሃማኖታዊ ሥርዓት ታስገባለች፤ እምቢ የሚሉትንም ታሳድዳለች።
- “ለሞቱ የሆነውም ቍስል ተፈወሰለት ለፊተኛው አውሬ ምድርና በእርሱ የሚኖሩት እንዲሰግዱለት ያደርጋል” ራዕይ 13፡12። አሜሪካ የዓለም መንግሥታትን በመምራት ሐሳዊ ክርስቶስ ለሆነው የጳጳሳዊ ኃይል እንዲሰግዱ ወደማስገደድ ሥራ ውስጥ

ትገባለች። (ሐሳዊ ክርስቶስ ማለት ሐሰተኛ ክርስቶስ ወይም ጸረ ክርስቶስ ማለት ብቻ ሳይሆን የክርስቶስ ቦታ ለኔ ይገባኛል ማለትም ነው)። ከጥንት ጀምሮ የነበረው አንዱና ዋንኛ ጉዳይ አምልኮ ነበር። የሰው ልጅ ማንን ይታዘዛል፤ ለማን ይሰግዳል



የሚለው ጥያቄ ባለንበት የመጨረሻ ዘመን የሰዎችን ዘላለማዊ ዕጣ ፈንታ የሚወስን ጉዳይ ይሆናል። ከዚህ አንጻር ሰዎች ለማን ይሰግዳሉ? ለሐሳዊው መሢሕ (ጳጳሳዊ ሥርዓት) ወይስ ለክርስቶስ እውነተኛው መሢሕ? የሚለው ለሰዎች በግልጽ የሚቀርብ ይሆናል። ሰይጣን በረቀቀ ስልት ድንቅንና ተዓምራትን በማድረግ (ራዕይ 13፡13-14)፤ እጅግ ብዙዎችን ያሳስታል፤ ያታልላል (ራዕይ 13፡3)። ይህንን እንቅስቃሴ አንቀላቀልም፤ አንቀበልም የሚሉ መናፍቃን፣ ጽንፈኛ፣ ተቃዋሚ፣ ጸረኅብረት፣ አመጸኛ፣ ወዘተ ተብለው ይኮነናሉ፤ ለሞት ተላልፈውም ይሰጣሉ። ይህ በራዕይ 13፡11 በበግ ተመስሎ የቀረበው

የአሜሪካ መንግሥት በራዕይ 19፡ 20፤ 20፡10 "ሐሰተኛው ነቢይ" ተብሎ እንደተጠራ እናነባለን (ራዕይ 19፡20፤ 20፡10)። ምክንያቱም ብዙዎችን ለማሳሳት ሰይጣን የሚከተለው ቀላሉ መንገድ መንፈሳዊና የሚታመን ሆኖ በመቅረብ ነው። ምናልባት አሁን ላይ ሆነን ይህንን ስናነብ ይከሰታል ብለን ለማመን ይከብደን ይሆናል። በትንቢተ ዳንኤል 2 እንደምንመለከተው በምስሉ የተጠቀሱት መንግሥታት በእርግጠኝነት እንደሚነሱና እንደሚወድቁ፤ በመጨረሻም እኛ ያለንበት ዘመን እንደሚደርስ ይህንንም ልክ እንደተተነበየው ሲፈጸም ተመልክተናል። ጌታችን ኢየሱስ ይህንን ብሏል፤ "ከሆነም በኋላ ታምኑ ዘንድ አሁን አስቀድሞ ሳይሆን ነግሬአችኋለሁ"(ዮሐ. 14፡29)።

❖ "የሰይፍም ቍስል ለነበረውና በሕይወት ለኖረው ለአውሬው ምስልን እንዲያደርጉ በምድር የሚኖሩትን ይናገራል" (ራዕይ 13፡14)። አሜሪካ ከባህር ለወጣውና ቁስሉ ለተፈወሰለት አውሬ (ጳጳሳዊ ሥርዓት) ሃይማኖታዊ ሕግጋትን ትደነግጋለች። የጨለማው ዘመን በሚባለው ወቅት ዓለምን ሲቆጣጠር በነበረው ጳጳሳዊ ሥርዓት ዘመን እንደነበረው አሁንም እንዲሁ ሃይማኖትን ከመንግሥት ጋር በማጋባት አሜሪካ ምስለ ጳጳሳዊ ሥርዓትን ትዘረጋለች። በተለይ በአሜሪካ መንግሥት ውስጥ ዋና ዐምድ የሆነው ፕሮቴስታንትነት ይህንን ሃማኖታዊ ሥርዓት ለመመሥረት ትልቅ ሚና ይጫወታል፤ ከጳጳሳዊ ሥርዓትም ጋር "ጋብቻ" በመፈጸም የዓለም ሕዝብ ለጳጳሱ እንዲገዛ

በጥምረት ይሠራል። ይህ በሚሆንበት ጊዜ በናፖሊዮን ዘመን ቆስሎ የነበረው ጳጳሳዊ ኃይል ቁስሉ ተፈውሶ እንደ መካከለኛው ዘመን ዓለምን በቁጥጥሩ ሥር ያደርጋል።

- ❖ "ለአውሬውም ምስል የማይሰግዱለትን ሁሉ (ያስገድላቸዋል)" (ራዕይ 13፡15)። ዓለምን በኃያልነት የምትመራው አሜሪካ ለዚህ ለጳጳሳዊ ሥርዓት የሚቆመውን ምስል "አንቀበልም"፣ "አንሰግድም" የሚሉ ሁሉ እንዲገደሉ የዓለምን መንግሥታት ታስተባብራለች። የዓለም መንግሥታትም አንታዘዝም ባዮችን ለመግደል የሚያስችል የሞት አዋጅ ያውጃሉ። የእነዚህ አንታዘዝም ባዮች ዋንኛ ጥፋት የሚሆነው የምናመልከው ኃያሉን ፈጣሪ አምላክ እግዚአብሔርን ብቻ ነው ማለታቸው ይሆናል። ይህ ዓለምአቀፋዊ ኅብረት "ታላቂቱ ባቢሎን" ተብሎ ይጠራል። ይህ ዓለምአቀፋዊ ኅብረት በአስገዳጅነት ለሚያወጣው ትዕዛዝና ሥርዓት አንታዘዝም የሚሉትን ሁሉ በቁጥጥር ሥር የሚያውልበትንና የሚያስገድድበትን፤ እምቢተኞችን የሚገድልበትን ሥርዓት ይዘረጋል።

## 8. ሞት የሚታወጅበት ዋናው ትዕዛዝ በምን ላይ ያተኮረ ነው?

"የአውሬው ምስል ሊናገር እንኳ ለአውሬውም ምስል የማይሰግዱለትን ሁሉ ሊያስገድላቸው፥ ለአውሬው ምስል ትንፋሽ እንዲሰጠው ተሰጠው። ታናናሾችና ታላላቆችም ባለ ጠጎችና ድሆችም ጌታዎችና ባሪያዎችም ሁሉ በቀኝ እጃቸው ወይም በግምባራቸው ምልክትን እንዲቀበሉ፥ የአውሬውም ስም ወይም የስሙ ቍጥር ያለው ምልክት የሌለበት ማንም ሊገዛ ወይም ሊሸጥ እንዳይችል ያደርጋል። ጥበብ በዚህ አለ" (ራዕይ 13፡15-17)።

የመጨረሻው ዘመን ትኩረት የሚያደርግበት ዋናው ጉዳይ አምልኮ ይሆናል። ይህም ደግሞ አውሬውንና ምልክቱ የሆነውን የእሁድ ሰንበትነት በመቀበል ለእርሱ መስገድ፤ ወይም የቅዳሜ ሰንበትነት በመቀበል ጌታ ኢየሱስን ማክበርና ለእርሱ መስገድ ይሆናል። ይህ የቀን ወይም አንድን ቀን ከሌላው አስበልጦ የማየት ጉዳይ ሳይሆን እግዚአብሔር ያዘዘውን ባይገባን እንኳን መታዘዝ አለብኝ ብሎ ከመቀበልና ለእርሱ ክብር ከመስጠት ጋር የተያያዘ ነው። የሰንበት ቀን የአምላካችንን ፈጣሪነት ብቻ ሳይሆን አዳኝነቱንም የምታሳይ ነች። በዚያች ቀን እርሱን በልዩ ሁኔታ የምናከብርበትና ከእርሱ ጋር የምንገናኝበት ነው። በሌሎቹም ቀናት ይኸው ግንኙነታችን አለ፤ አስፈላጊም ነው። የሰንበት ቀን ግን ከሥራ፣ ከሳምንታዊ ጉዳዮችን፣ ከትምህርት፣ ወዘተ በመቆጠብ ሙሉውን 24 ሰዓት ባምላካችን በመታመን ስለ እርሱ ብቻ በማሰብ የምናሳልፈው ነው። ይህንን ግልጽ ትዕዛዝ አልቀበልም ብሎ የጳጳሳዊ ኃይል በራሱ ላቋቋመው የእሁድ ሰንበት መገዛትና ያንን ማክበር ከአምላክ ሕግ ይልቅ ለሰው መገዛት ነው፤ ለጌታ ከመስገድ ይልቅ ለአውሬው መስገድ ነው። የሮም ጳጳሳዊ ሥርዓት የእሁድ ሰንበትነት አስመልክቶ ሲናገር ይህንን ይላል፤ "ቤተክርስቲያኗ ሰንበትን (ከቅዳሜ) ወደ እሁድ ቀይራለች፤ በመሆኑም ዓለም ሁሉ አምልኮውን በዚያን ቀን በመፈጸም ለካቶሊክ ቤተክርስቲያን ትዕዛዝ በጸጥታ በመታዘዝ ይሰግዳል" (ምንጭ፤ Hartford Weekly Call, February 22, 1884)።

## 9. በርግጥ መንግሥት መግዛትና መሸጥን መከልከል ይችላል?

በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት መግዛትን በተመለከተ በዜጎች ላይ ቁጥጥር ተደርጎ ነበር፤ ሰዎች ስኳር፣ ነዳጅ እና የመሳሰሉትን በራሽን እንዲገዙ የተደረገበት ወቅት ነበር። ዕቃዎችን በሚገዙበት ጊዜ ማኅተም የተመታባቸውን ኩፖኖች የያዙ ብቻ ነበሩ መግዛት የሚችሉት። ማኅተም ከተደረገባቸው ኩፖኖች ውጪ ጥሬ ብር እንኳን ምንም መግዛት የማይችል ዋጋ ቢስ ሆኖ ነበር።

ባለንበት ዘመን ነገሩ ሁሉ በኮምፒውተር ቁጥጥር የሚደረግበትና ሰዎች በጣት አሻራቸውና በሚሰጧቸው ልዩ ግላዊ የመለያ ቁጥሮች አማካኝነት ማንነታቸው የሚታወቅ በመሆኑ ቁጥጥር ለማድረግ ብዙም የሚከብድ አይሆንም። በዚህ መሠረት መንግሥት ከሃይማኖት መሪዎች ጋር በመስማማት የሚያወጣውን ሕግ አንታዘዝም የሚሉ ሁሉ በቀላሉ በኮምፒውተር ቋት ውስጥ በእምቢተኝነት ተመዝግበው የትም ቦታ ምንም መግዛት እንዳይችሉ ማድረግ ይቻላል። ይህ አንድ

መላምት ሲሆን ይህ መግዛትና መሸጥ የመከልከል ሥራ በእርግጠኝነት እንዴት እንደሚከናወን ማንም አሁን የሚያውቀው አይደለም። እርግጠኛ የምንሆንበት ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል የተናገረው የሚፈጸም መሆኑን ነው።

### ሁለቱ ገናና ኃይላት

በራዕይ 13 ሁለት ዓለምአቀፋዊ ኃይላት እንዳሉ እናነባለን፤ አንዱ ከባህር የሚወጣ ሲሆን ሌላው ደግሞ ከምድር የሚወጣ ነው። እነዚህ ልዕለኃያላን ባለንበት የመጨረሻ ዘመን የዓለማችንን አጠቃላይ የኃይል አሰላለፍ የሚቆጣጠሩና የሚወስኑ ናቸው። እነዚህም የሮም ቤተክርስቲያን (ቫቲካን) እና አሜሪካ ናቸው። አሜሪካ ቫቲካንን በመርዳት ዓለም የጳጳሳዊ ሥርዓትንና በእርሱ በኩል የሚወጡትን ሕግጋት እንዲፈጽም ታደርጋለች። በሌላ አነጋገር ለአውሬው እንዲሰግዱና ምልክቱንም እንዲቀበሉ ታደርጋለች። ይህንን አንቀበልም የሚሉትንም በሞት እንዲቀጡ የሚደነግግ ሕግ በማስወጣት በኩል አሜሪካ ቁልፍ ሚና ይኖራታል። ጳጳሳዊ ሥርዓት የጨለማው ዘመን በሚባለው ወቅት ኃይማኖታዊ ደንቦችን በመደንገግ ሰዎች እንዲታዘዙ ሲያደርግ የነበረ ሲሆን የሮምንና የሌሎች መንግሥታትን ሥልጣን በመጠቀም ደግሞ እነዚህን ኃይማኖታዊ ድንጋጌዎችን አንቀበልም የሚሉትን ሲያስቀጣና ሲያስገድል እንደነበር ታሪክ ይመሰክራል። በዚህም ዘመን ተመሳሳይ ተግባር እንደሚፈጽም ይህ ጥናት ይነግረናል።




### 10. ባለንበት ዘመን ጳጳሳዊ ሥርዓት ምን ያህል ብርቱና እና ተጽዕኖ ፈጣሪ ነው?

ቫቲካን የሚገኘው ጳጳሳዊ ኃይል በልዩ ሁኔታ የመንግሥትንና የኃይማኖትን ሥልጣን አጣምሮ የያዘ የዓለማችን ብቸኛ የሚባል ሥርዓት ነው። ይህም በዓለም ላይ በተለየ ሁኔታ ተጽዕኖ ለመፍጠር የሚያስችል ሥልጣንን አጎናጽፎታል። የቫቲካን የበላይ ኃላፊና መሪ ሊቀ ጳጳሱ ሲሆኑ እርሳቸው በዚያው ሥልጣናቸው "ቅዱስ አባት"፣ "ብፁዕ ወቅዱስ" እየተባሉ የሚጠሩ የኃይማኖት መሪም ናቸው። በዓለም የሚገኙ አገራት በሙሉ ሊባል በሚችል ሁኔታ አምባሳደሮቻቸው በቫቲካን ይገኛሉ። ቫቲካንም እንደ አገር አምባሳደሯን በየአገራቱ አስቀምጣለች። አንዳንድ ዕውነታዎችን አለፍ አለፍ እያልን ብንመለከት፤

❖ ሊቀ ጳጳስ ፍራንሲስ እኤአ በ2015 በአሜሪካ ያደረጉት ጉብኝት ፖለቲካዊም ሃይማኖታዊ እንዲያውም "ሐዋሪያዊ" ነበር። እንደ አንድ የአገር ፖለቲካ መሪ በአሜሪካ የእንደራሴዎች ምክርቤት በመገኘት በዓለም ማኅበረሰባዊና ፖለቲካዊ እንዲሁም ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች በተለይም የአካባቢ ጥበቃን በተመለከተ ንግግር አድርገው ነበር። በተለያዩ ከተሞች ደግሞ ሥርዓተቅዳሴ በማካሄድ ልዩ ፕሮግራሞችንም መርተው ነበር። ካርዲናል ጢሞቴዎስ ዶላን ሲቢኤስ በተሰኘው የአሜሪካ ቴሌቪዥን ጣቢያ በወቅቱ ይህንን ብለው ነበር፤ "እርሳቸው (ፖፕ ፍራንሲስ) ጳጳሳዊ ሥልጣንና ክብር ትኩረት እንዳይሰጣቸው ባደረጉ ቁጥር ብዙ ሰዎች እየሰሟቸውና ትኩረት እየሰጧቸው ይሄዳሉ" (ምንጭ፤ Cardinal Timothy Dolan፤ CBS This Morning, September 22, 2015)

❖ የቫቲካን ዋንኛ ሃሳብ የክርስቲያኑን ዓለም አንድ ማድረግ፣ ማዋኃድ ነው። እኤአ በ2014ዓም ሊቀጳጳስ ፍራንሲስ በቅዱስ ጳውሎስ ባሲሊካ (ግዙፍ ቤ/ክ) ከኦርቶዶክስ፣ ከአንግሊካን፣ ከሉተራን፣ ከሜቶዲስትና ከሌሎች

አብያተክርስቲያናት ከተውጣጡ ተወካዮች ጋር እርሳቸው የመሩት የኅብረት ስብሰባ ተካሄዷል። በወቅቱ ክርስቲያናዊ ኅብረት ትልቅ ትኩረት የተሰጠው ሲሆን ሊቀጳጳስ ፍራንሲስም ይህንን ብለው ነበር፤ "በቤተክርስቲያናት መካከል ያለውን ልዩነት ተፈጥሮአዊና መሆን ያለበት አድርጎ መውሰድ ተቀባይነት የሌለው ነው፤ ምክንያቱም መከፋፈል የክርስቶስን አካል የሚያቆስልና አማኙ የተጠራበትን ለዓለም ሊሰጥ የሚገባውን ምስክርነት የሚያንሸዋርር ነው" (ምንጭ፤ Catholic Herald, January 27, 2014)

- የዓለምን ሰላም በተመለከተ መሪዎች በቀዳሚነት የሚያማክሩትን ሊቀጳጳስ ፍራንሲስን ነው። ከጥቂት ዓመታት በፊት ፖፕ ፍራንሲስ በቫቲካን ከእስራኤልና ፍልስጤም መሪዎች ጋር የጸሎት ጉባዔ አካሂደዋል። ከዚህ ሌላ በላቲን አሜሪካ ያላቸውን ከፍተኛ ተቀባይነት በመጠቀም (የተወለዱትም እዚያው ነው) በኩባና በአሜሪካ መካከል ለበርካታ ዓመታት የዘለቀውን ልዩነት በማጥበብ ወደ ስምምነት እንዲመጡ አድርገዋል። (ምንጭ፤ Sylvia Poggioli, National Public Radio, April 14, 2016 ዘገባ)



- የማንኛውም አገር መሪ ወደ አሜሪካ ለጉብኝት ሲመጣ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት በአውሮጵላን ማረፊያ በመሄድ አቀባበል አያደርግም። ነገርግን በ2015 ዓም ሊቀጳጳስ ፍራንሲስ ወደ አሜሪካ በመጡ ጊዜ በወቅቱ በሥልጣን ላይ የነበሩት ፕሬዚዳንት ኦባማ ጳጳሱ በመጡበት የአሜሪካ የአየር ኃይል በመሄድ ደፋዊ አቀባበል አድርገውላቸዋል። ይህም በኋይት ሃውስ (ነጩ የአሜሪካ ቤተመንግሥት) አስደተዳደር የተወሰደ እርምጃ መንግሥትና የአሜሪካ ሕዝብ ለጳጳሱ ያላቸውን ታላቅ አክብሮት ያሳዩበት ተደርጎ ተወስዷል። ከዚህ ሌላ በአሜሪካ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የሮም ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ሊቀጳጳስ ፍራንሲስ በአሜሪካ ጣምራ ምክርቤት ፊት በመቅረብ ንግግር አድርገዋል። (ምንጭ፤ Irish Daily Mail, September 23, 2015)

## 11. ባሁኑ ዘመን አሜሪካ ምን ያህል ብርቱና ተጽዕኖ ፈጣሪ ነች?

ባለንበት ዘመን አሜሪካ ብቸኛዋ የዓለም ልዕለ ኃያል ነች። አንዳንድ ጠቋሚ መረጃዎችን እንመልከት፤

- "በቀጣይ ባሉት በርካታ ዓመታት በብዙ ዘርፎች አሜሪካ ቀዳሚ ኃያል አገር ሆና ትቀጥላለች"– Ian Bremmer, Time magazine, May 28, 2015
- "በጦርነትና በሰላም መካከል ያለው ወሳኝ ልዩነት ... መልካም አስተሳሰብ፣ ከረር ያሉ ቃላት፣ ወይም የላቀ ትብብርና ስምምነት ሳይሆን አሜሪካ እስከ ምድር ጥግ ለመድረስ የምትዘረጋው ብቃት፣ ተዓማኒነትና ዓለምአቀፋዊነት ነው" – Senator John McCain, November 15, 2014
- "አሜሪካ በጣም አስፈላጊ ወይም ምትክ የሌላት አገር ናት እንደዚህ ሆናም ትቀጥላለች፤ ይህ ለበርካታ መቶ ዓመታት የኖረ ሐቅ ነው፤ ወደፊትም ለበርካታ መቶ ዓመታት ሐቅ ሆኖ ይቀጥላል" – President Barack Obama, May 28, 2014.

❖ የቀድሞው የፈረንሳይ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሁበርት ቬርዲን በፓሪስ በተደረገ ስብሰባ ላይ ሲናገሩ “አሜሪካ ማለት በሁሉም ዘርፍ የላቀ የበላይነት ያላት ልዕለኃያል (‘hyperpower’) አገር ነች” ብለዋል – The New York Times, February 5, 1999

ምንም እንኳን እንደ ሩሲያና ቻይና ያሉ አገራት የአሜሪካንን የበላይነት የሚገዳደሩ ኃይላት መሆናቸው ባይካድም አሜሪካ የሚቃጣባትን ማንኛውም ጥቃት ፈጥና ለመቋቋምና ለመመከት የመቻሏ ጉዳይ ለጥያቄ የሚቀርብ አይደለም። በመሆኑም በዓለማችን ላይ ከፍተኛ የበላይነት ኖሯት መቀጠሏ የማይቀር ነው። ስለሆነም በዓለም ሰላም ወይም በጸጥታና መረጋጋት ስም ዓለምን የሚያስተባብር ድንጋጌ ቢወጣ ወደፊት የሚነሱትም ሆነ አሁን በሥልጣን መንበር የሚገኙት ፕሬዚዳንት ሕጉን ከመደገፍና የአሜሪካንን ተፅዕኖ በመጠቀም ሕጉን ከማስፈጸም ወደኋላ አይሉም።

### 12. ዓለምን አንድ የማድረጊያና ይህንን የሚቃወሙትን ደግሞ ጸጥ የማሰኛ ምክንያቶች ምን ይሆናሉ?

ዓለምን አንድ ለማድረግ በጥቅም ላይ የሚውለው መንገድ አንድ ብቻ ነው ለማለት አይቻልም። በአንድ መንገድ ብቻ 8 ቢሊዮን የሚሆነውን የዓለም ሕዝብ አንድ ለማድረግ አይቻልም። ነገር ግን በቅርቡ እንዳየነው የኮሮና ቫይረስ (ኮቪድ-19) ዓለም በአንድ መንገድ እንዲጓዝ አድርጎታል፤ ከበርሊን እስከ ቤንሻንጉል፤ ከፓሪስ እስከ ቦረና፤ ዓለም በአንድ ቋንቋ ሲናገር፣ መረጃ ሲለዋወጥ፣ ሕግ ሲያወጣ፣ ሕግ ሲያስፈጽም፣ ወዘተ ታይቷል። ይህ በማንም ሰው ስሌት ይሆናል ተብሎ ያልተጠበቀ ክስተት ነው። ስለዚህ ወደፊት የሚሆኑትን ከወዲሁ ለመናገር ቢከብድም ከሚታዩት ሁኔታዎች ጥቂቶቹን እንዘርዝር፤

❖ አሸባሪነት

❖ ከወንጀል መበራከትና ያንን ተከትሎ የሚነሳው ብጥብጥ

❖ አደንዛዥ ዕፅ ዝውውርና በዚያ ላይ የሚታወጀው ጦርነት

❖ የኢኮኖሚ ቀውስ

❖ ወረርሽኝ (እንደ ኮሮና ቫይረስ ያሉ)

❖ ከጽንፈኛ መንግሥታት የሚነዛው የኑክሊየር ዛቻ

❖ የፖለቲካ ሙስና

❖ የፍትህ መጨናገፍ (ኢፍትሐዊነት)

❖ የማኅበራዊና የፖለቲካ ውዝግብ

❖ የግብር መጨመር

❖ የግብረገብነት (የሞራል) መዝቀጥና መረን የለቀቀ ብልግና (በፍትወት መቃጠል)

❖ ዓለምአቀፋዊ የተፈጥሮ አደጋ

❖ የአካባቢ ብክለት

❖ አክራሪነትና ጽንፈኝነት

እነዚህንና የመሳሰሉትን ለመዋጋት በሚል የሚወጡ



ሕግጋት በመብት ገፈፋ ላይ የሚጫወቱት ሚና ቀላል አይሆንም። አሸባሪነትን፣ ሕገወጥነትን፣ ኢግብረገባዊነትን፣ ልቅነትን፣ ኢፍትሐዊነትን፣ ድህነትን፣ ሙስናን፣ ወዘተ ላይ የሚታወጀው ጦርነት አስፈላጊ ቢሆንም ይህንኑ ተከትሎ የሚወጡ አፋኝ ሕግጋት የመብት ጥሰት በማስከተል በሌሎችም ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት እንዲኖራቸው ሊደረግ ይችላል።

### 13. የዓለም ችግር እየተባባሰ ሲሄድ ሰይጣን ብዙሃኑን ለማሳሳት ምን ያደርጋል?

“እሳትንም እንኳ ከሰማይ ወደ ምድር በሰው ፊት እስኪያወርድ ድረስ ታላላቆችን ምልክቶች ያደርጋል። በአውሬውም ፊት ያደርግ ዘንድ ከተሰጡት ምልክቶች የተነሣ በምድር የሚኖሩትን ያስታል፤ የሰይፍም ቍስል ለነበረውና በሕይወት ለኖረው ለአውሬው ምስልን እንዲያደርጉ በምድር የሚኖሩትን ይናገራል” (ራዕይ 13፡13-14)።

በዓለማችን እንደምናየው ሃይማኖት ትልቁ የሰዎችን ህይወት የሚነካ ጉዳይ ሆኗል። በየቦታው የሃይማኖት መነቃቃትና የተዓምራትና የፈውስ አገልግሎቶች እየተሰጡ ይገኛሉ። የብልጽግና ወንጌልም በድህነትና በመከራ የሚማቅቀውን ህዝብ የተስፋ ዳቦ እያበላ የእንቅስቃሴውን አራማጆች ኪስ እያደለበ ይገኛል።

ይህ በተለይ በአሜሪካ አገር በቀላሉ እየተስፋፋ የመጣ ሲሆን አሜሪካ ከአነሳሷ ጀምሮ ሃይማኖትን




(በተለይ ፕሮቴስታንትነትን) መሠረት ያደረገች አገር በመሆኗ ለሃሰተኛ መነቃቃት በጣም ቅርብ የሆነች አገር ናት። ከላይ እንደተመለከትነው አሜሪካ ከምድር በወጣው በግ መሰል አውሬ ብቻ ሳትሆን በሐሰተኛ ነቢይ ጭምርም ትመሰላለች። ይህ ደግሞ ብዙዎችን ወደ ስህተት ለመምራት ዓይነተኛ መንገድ የሚከፍት ይሆናል።

ሌላው አሜሪካ ባላት ሥልጣን በመጠቀም ዋናዋ ዓላማ ለጳጳሳዊ ሥርዓት ምስል ማቆም ስለሆነ የእሁድ ሰንበትነት በአዋጅ እንዲጸድቅ በማድረጉ ሒደት ቁልፍ ሚና ትጫወታለች። እሁድ ዓለምአቀፋዊ የዕረፍት ቀን ሆኖ እንዲከበር የሚወጣውን ሕግ የማይታዘዙ፤ እውነተኛውንና ሰባተኛውን ቀን ሰንበት የሚያከብሩ መግዛትና መሸጥ እንዳይችሉ የሚገደዱበት ሁኔታዎች እንዲመቻች በማድረግ በኩል አሜሪካ በቀዳሚነት ከሌሎች አገራት ጋር በመሆን የምትከወነው ይሆናል። የዓለም ችግር ሲፋፋም፤ ሰዎች ወደ "አምላካቸው" እንዲጮኹ ሲደረግ፤ በአንድነት እንዲያመልኩ ሁኔታዎች ሲመቻቹ፤ ከሌሎች ላለመለየትና ዒላማ ውስጥ ላለመግባት ይህንን ሃሰተኛ እንቅስቃሴ የሚቀላቀሉ ጥቂት አይሆኑም።

አምነውበትም ይሁን ፈርተው አውሬውን ምልክት በግምባራቸው ወይም አቀኝ እጃቸው ይቀበላሉ።

## 14. ሃሰተኛው መነቃቃት ሲፋፋም እውነተኛውስ እንደተዳፈነ ይቀራል?

"ከዚህ በኋላ ታላቅ ስልጣን ያለው ሌላ መልአክ ከሰማይ ሲወርድ አየሁ፥ ከክብሩም የተነሣ ምድር በራች" (ራዕይ 18፡1)።

በማቴዎስ 24፡14 እንደምናነበው "ለአህዛብ ሁሉ ምስክር እንዲሆን ... ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል"። ይህ ወንጌል በሚሰበክበት ጊዜ ምድር በወንጌል ከሚመጣው ብርሃን የተነሣ ትበራለች። በተለይም እግዚአብሔር በራዕይ 14፡6-14 ላይ የተናገረው ሦስትዮሽ ይዘት ያለው መልዕክት የዓለም ሕዝብ ሁሉ የሚሰማውና ምርጫውን የሚያስተካክልበት ይሆናል።

ይህ ምድርን የሚያበራ ወንጌል በሚሰበክበት ጊዜ እጅግ ብዙዎች ከዚህ በፊት ሰምተውት የማያውቁትን እውነት በመስማት በደስታ ይቀበሉታል። በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተከፈለውን መስዋዕትነት በመቀበል ራሳቸውን ለዳግም ምፅዓቱ ያዘጋጃሉ። አውሬውን አንሰግድም፤ ለምስሉ አንሰግድም፤ ምልክቱንም አንቀበልም በማለት በገሃድ ለእግዚአብሔር ያላቸውን ታማኝነት ይገልጻሉ። በዚህም የእግዚአብሔርን ማኅተም ይቀበላሉ፤ ለዘላለማዊ መንግሥቱም ይታተማሉ (ራዕይ 7፡2-3)።

ይህንን መልዕክት የሚቀበሉ እምነታቸው ሊፈተን፤ ሊሰደዱና ለመኖር እስኪያቅታቸው ድረስ መግዛትና መሸጥ እንዳይችሉ ሊገደዱ ይችላሉ፤ የእግዚአብሔር ቃል ግን ይህንን ተስፋ ሰጥቶናል፤ "እርሱ ከፍ ባለ ስፍራ ይቀመጣል፤ ጠንካራ አምባ መጠጊያው ይሆናል፤ እንጀራም ይሰጠዋል፥ ውኃውም የታመነች ትሆናለች" (ኢሳይያስ 33፡16)፤ "የእግዚአብሔር መልአክ በሚፈሩት ሰዎች ዙሪያ ይሰፍራል፥ ያድናቸውማል" (መዝሙር 34፡7)።

### 15. ሁኔታው ሲፋፋም በራዕይ 13፡14-15 በተጠቀሰው መሠረተ ሰዎችን ለማሳመን የሚተገበረገው ዋነኛ ስልት ምንድነው?

በእግዚአብሔር ያመኑትን ሳይቀር እምነታቸውን የሚፈትን ታላቅ ድንቅና ተዓምራት ይካሄዳል። በመጨረሻው ጊዜ ሰዎች እውነትን እያወቁ ለእውነት በመቆም ውሳኔያቸውን እያከረሩ ሲመጡ እነሱን ለማሳመን እጅግ አስደናቂ ተዓምራትና ድንቅ ይከናወናሉ (ማቴዎስ 24፡24)። ሰይጣን እና አጋንንቱ የሞቱ ወገኖቻችን እና ከመጽሐፍ ቅዱስ የታወቁ የእግዚአብሔር ነቢያትንና ሃዋርያትን በመምሰል ይገለጣሉ፤ ብዙዎችንም ያስታሉ (ራዕይ 18፡23)። ይህንንም በሚያደርጉበት ጊዜ እነዚህ አሳሳች አጋንንትና የሰይጣን ተወካዮች እግዚአብሔር ልኮን ነው የመጣነው በማለት ነው ብዙዎችን በመዋሸት የሚያታልሉት (ዮሐ. 8፡44)።

ሰይጣን ክርስቶስን በመምሰል ይገለጣል፤ አጋንንቱም የክርስቲያን አገልጋይ ሆነው ይታያሉ፤ ሰይጣን የብርሃን መልአክ መስሎ ይገለጣል ይላል 2 ቆሮንቶስ 11፡13-15። ይህ ብቻ ሳይሆን ጌታችንን ኢየሱስ መስሎ በግልጽ በመታየት ብዙዎች እንዲሰግዱለት ያደርጋል (ማቴዎስ 24፡23-24)። ይህንን በሚደርግበት ጊዜ የእግዚአብሔርን ሕግጋት ሰንበትንም ጨምሮ መቀየር በማስፈለጉ ምክንያት እንደተቀየረና ሰዎች በዚህ መልኩ እንዲታዘዙት የሚችለውን ማሳመኛ ሁሉ ይጠቀማል፤ ብዙዎችም ለውሸቱና ለቅጥፈቱ እጅ ይሰጣሉ።

በቢሊዮን የሚቆጠሩ የዚህ ማታለያ ሰለባ ይሆናሉ፤ በቢሊዮን የሚቆጠሩ የዓለማችን ሰዎች ሰይጣንን በእውነት ኢየሱስ ነው ብለው ይቀበላሉ። ጌታችንን በምድረበዳ በፈተነው ጊዜ ሰይጣን ወድቀህ ስገድልኝ እንዳለው (ማቴዎስ 4፡9)፤ በዚህ ወቅትም ሰዎች እንዲሰግዱለት ያደርጋል፤ “ምድርም ሁሉ አውሬውን እየተከተለ ተደነቀ” (ራዕይ 13፡3)። አውሬውን የሚያንቀሳቅሰውና ትዕዛዝ እየሰጠ የሚመራው ዘንዶው የተባለው ሰይጣን ስለሆነ ለአውሬው የሚሰጥ ማንኛውም ስግደት ለዘንዶው እንደ ገጸበረከት የሚቀርብ ነው። የእግዚአብሔር ልጆች ግን አይታለሉም፤ ለሰይጣን ማሳሳቻ አይበገሩም፤ ማንኛውንም ነገር በቃሉ ይፈትናሉ (ኢሳይያስ 8፡19-20፤ 2ጢሞቴዎስ 2፡15)። የእግዚአብሔር ሕግ መቼም ቢሆን የማይለወጥ ነው (ማቴዎስ 5፡18)። ጌታችን ወደ ምድር ዳግም ሲመጣ ዓይን ሁሉ ያየዋል (ራዕይ 1፡7)፤ እንጂ በምድር እየተንጎራደደ ሕሙማንን አይፈውስም፤ እግሩም ምድርን አይረግጥም፤ ይኸው እኔ ኢየሱስ ክርስቶስ ነኝ ብሎ አዋጅ አያስነግርም፤ ሰበር ዜና አያሰማም (1ተሰሎንቄ 4፡16-17)።

### 16. ከመጨረሻው ዘመን አደገኛ ማታለያ እንዴት እንጠበቅ?

- ❖ ሁሉንም ትምህርት በእግዚአብሔር ቃል በመፈተን (2ጢሞቴዎስ 2፡15፤ የሐዋሪያት ሥራ 17፡11፤ ኢሳ. 8፡20)፤
- ❖ በጌታችን የተገለጸውን እውነት ከልብ በእምነት በመከተል (ዮሐንስ 7፡17)፤
- ❖ ከኢየሱስ ጋር በቅርብ በመኖር፤ ከእርሱ ባለመለየት (ዮሐንስ 15፡5)፤

## ተጨማሪ ጥያቄዎች፤

### 1. ለዘመናት እውነትን ሳይሰሙ የቆዩ ሰዎች በመጨረሻው ሐሰተኛውን ትምህርት ተቀብለው መጥፋታቸው እንዴት ትክክል ይሆናል?

የመጨረሻውን ጊዜ በሚሆንበት ወቅት ማንም ሰው እውነቱን ሳይሰማ እና መወሰን ሳይችል የስህተትን መንገድ ሊመርጥ አይችልም። እግዚአብሔር አመጻኛ አምላክ አይደለም። ሁሉም ሰው እውነትን እንዲሰማ ያደርጋል፤ ቃሉም የሚመሰክረው ይህንኑ ነው (ማርቆስ 16፡15፤ ዮሐንስ 1፡9)። በራዕይ 14፡6-12 የተጻፈው ሦስትዮሹ መልዕክት ለሁሉም ሰው በግልጽና ምንም በማያሻማ ሁኔታ ይቀርባል። ከዚህ በኋላ ነው ሰዎች የአውሬውን ምልክት የሚቀበሉት እና ወደ ጥፋታቸው የሚሄዱት፤ ምክንያቱም ክርስቶስን መከተል ዋጋ ያስከፍላል፤ መስዋዕትነት አለው።

### 2. በራዕይ 16፡12-16 የተጠቀሰው የአርማጌዶን ጦርነት ምንድነው? የት፣ መቼና ከማን ጋር ይደረጋል?

የአርማጌዶን ጦርነት በክርስቶስና በሰይጣን መካከል የሚደረግ የመጨረሻው ጦርነት ነው። የሚካሄደውም በዚህች ምድር ላይ ሲሆን ልክ የመጨረሻው ጊዜ ከመጠናቀቁ በፊት የሚፈጸም ይሆናል። ነገርግን ጦርነቱ በጌታችን ዳግም ምፅዓት

ምክንያት ይቋረጣል፤ ይጨናገፋል። ከዚያ 1,000 ዓመት ከተጠናቀቀ በኋላ በድጋሚ ይነሳል፤ ሆኖም በዚህ ወቅት ኃጥአን ከሰይጣንና መላዕክቱ ጋር በመሆን አዲሲቱን ኢየሩሳሌም ለመውረር በሚያነሱት ጦርነት እሣት ከሰማይ ወርዶ ይበላቸዋል፤ ጦርነቱም ይጠናቀቃል።

## “አርማጌዶን” ምን ማለት ነው?

ይህ አርማጌዶን የተባለው “ሁሉን በሚችል አምላክ ታላቅ ቀን የሚሆነው ጦርነት” ነው፤ ይህም የሚካሄደው ሁሉም ሰው በሚሳተፍበት ሁኔታ በክርስቶስና በሰይጣን መካከል ነው (ራዕይ 16፡12-16፤19)። “ከፀሐይም መውጫ ለሚመጡ ነገሥታት መንገድ እንዲሰናዳላቸው” የተባለው ለእግዚአብሔር አብና ለልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። “የፀሐይ መውጫ” የሚለው “ምስራቅ” ተብሎ የሚጠራው ሲሆን የሚያመለክተውም የእግዚአብሔርን የሰማይ መንግሥት ነው (ራዕይ 7፡2፤ ሕዝቅኤል 43፡2፤ ማቴዎስ 24፡27)። በዚህ ጦርነት ዓለም በሙሉ ይሳተፋል (ራዕይ 16፡14)፤ ጦርነቱም የሚከፈተው ጌታችን ኢየሱስንና እርሱን በሚከተሉ ላይ ነው (ራዕይ 17፡14፤ 19፡19)። የጦርነቱ ዋንኛ ዓላማም አውሬውን አናመልክም፣ ምልክቱንም አንቀበልም ያሉትን በማስወገድ ላይ ያነጣጠረ ነው (ራዕይ 13፡15-17)።

## የስህተት አሠራርና እውነትን መርገጥ

የእግዚአብሔርን መልዕክት ለመቀበል አሻፈረን የሚሉና እውነትን ሲቃወሙ የኖሩ ሁሉ ውሸትን ለመቀበል ሁኔታው የተመቻቸ ይሆንላቸዋል (2 ተሰሎንቄ 2፡10-12)። ከዚህም የተነሳ በተዘፈቁበት የሃሰት አሠራር ውስጥ ሆነው የእግዚአብሔር ሥራ ነው ብለው በማሰብ እውነተኞቹን የእግዚአብሔር ልጆች ለማጥፋት በርትተው ይሠራሉ። ቅዱሳን የጌታሰዎችንም “አክራሪ፤ ጽንፈኛ” ብለው በመሰየም የዓለምን ጥፋት የሚያልሙና የሚመኙ እንዲሁም በዓለምአቀፍ ደረጃ እየተካሄደ ያለውን መነቃቃት (ሃሰተኛውን) የሚቃወሙ አድርገው በመውሰድ የጥቃት ዒላማ ያደርጓቸዋል። ይህ ለሁለት ጎራ ክፍፍል የአርማጌዶን ዋነኛ የጦርነት ሃሳብ ይሆናል።

## የጌታችን ዳግም ምፅዓት ጦርነቱን ያስቆማል

የአርማጌዶን ጦርነት ዓለምአቀፋዊ ነው። መንግሥታት የእግዚአብሔርን ልጆች ለማጥፋት ይሞክራሉ፤ ጌታ አምላክ ግን ጣልቃ ገብቶ ይታደጋቸዋል። ከላይ በጥቅሱ እንዳነበብነው በምሳሌ የተጠቀሰው የኤፍራጥስ ወንዝ ይደርቃል (ራዕይ 16፡12)። ከዚህ በፊት እንዳጠናነው ውሃ በትንቢት ብዙ ሕዝብን ነው የሚያመለክተው (ራዕይ 17፡15)። የኤፍራጥስ ወንዝ መድረቅ የሚያመለክተው አውሬውን ሲደግፉ የነበሩ እጅግ በርካታ ሰዎች ለአውሬው (ለሰይጣን) ይሰጡ የነበረውን ድጋፍ የሚያቆሙ መሆኑን ነው፤ ሁሉ ነገር ይደርቃል።



የተመሠረተው ሃሰተኛ ጥምረት የእምቧይ ካብ ይሆናል (ራዕይ 16፡13-14 እና 19)፤ የክርስቶስ ዳግም መመለስ ጦርነቱን በማስቆም ለመከራ ተዳርገው የነበሩትን ልጆቹን ይታደጋል (ራዕይ 6፡14-17፤ 16፡18-21፤ 19፡11-20)።

## ጦርነቱ ከ1,000 ዓመት በኋላ እንደገና ይደረጋል

ሺሁ ዓመት ሲፈጸም ሰይጣን በእግዚአብሔርና በሕዝቡ ላይ በሚደረገው ጦርነት ዋና መሪ በመሆን ተከታዮቹን አስተባብሮ ለጦርነት ይነሳል። ከሺህ ዓመት በፊት ያቋረጠውን ጦርነት በማዘመን በልዩ ሁኔታ ኃይሉን አስተባብሮ የእግዚአብሔርን ከተማ ሊወርር ሲል እሣት ከሰማይ ወጥቶ እርሱንና ተከታዮቹን በሙሉ ያጠፋቸዋል።

### 3. ጌታችን ኢየሱስ “የሚገድላችሁ ሁሉ እግዚአብሔርን እንደሚያገለግል የሚመስልበት ጊዜ ይመጣል” ብሎ ነበር (ዮሐንስ 16፡2)። በርግጥ ይህ በዚህ ዘመን ይፈጸም ይሆን?

አዎ፤ በመጨረሻው ጊዜ በመንግሥታትና በሃይማኖት ድርጅቶች መካከል በሚፈጠረው ኅብረት ለእግዚአብሔር ልጆች የሚሰጠው ርኅራኄ ያከትማል። ሃሰተኛውን መነቃቃት በመቀበል ለእግዚአብሔር እየሠሩ የሚመስላቸው በርካቶች የእሁድ ሰንበት አምልኮን ይቀበላሉ። ከመነቃቃቱ ጋር በተያያዥነት የሚከሰቱት ድንቆችና ተዓምራት

ትክክለኛ ለመሆናቸው እንደ ማስረጃ ይቀርባሉ። ፈጽሞ ይድናሉ ተብለው የማይጠበቁ በሽታዎች ሊድኑ፣ ሙታንም ሳይቀሩ የተነሱ መስለው ሊታዩ ይችላሉ፤ ሃይማኖተኛ ይሆናሉ ተብለው የማይገመቱ ብዙዎች በዚህ መነቃቃት ምክንያት የእምነትን መስመር ተከትዬአለሁ እያሉ ሲናገሩ በየሚዲያው በስፋት የሚወራ ጉዳይ ይሆናል። ይህንን ዓይነቱን መነቃቃት የሚቃወሙ ፈጽሞ ተቀባይነት የማያገኙና ጸረ መነቃቃትና ተሃድሶ ተደርገው ይወሰዳሉ። በዚህ ሃሰተኛ መነቃቃት ውስጥ የሚገቡት ሰዎች እሁድን እንደ እውነተኛ ሰንበት ለመቀበል ብዙ የማይከብዳቸው ይሆናሉ። ይህንን ሃሰተኛ ትምህርት አንቀበልም የሚሉ በአሁኑ ዘመን "አክራሪ ትምህርት" ተከታዮች እንደሚባሉት በዚያም ጊዜ ከዚህ በበለጠ ይወነጀላሉ። ጸረ ሰላም፣ ጸረ አንድነት፣ ጸረ ወንድማማችነትና ጸረ ኅብረት ተብለው ይፈረጃሉ። ከዚህ ጽንፈኛ አቋማቸው በመላቀቅ ዓለምአቀፋን መነቃቃት እንዲቀላቀሉ ጥሪዎች ይቀርቡላቸዋል። አንዳንዶች እሺ ብለው ጥያቄውን የሚፈጽሙ ሲሆን እምቢ የሚሉትን ግን ከሃዲ፣ ጽንፈኛ፣ ግትር፣ አውቃለሁ ባይ፣ ትምክህተኛ፣ አደገኛ አክራሪ፣ ወዘተ ብለው በመፈረጅ እነዚህን ካላጠፋን ሰላም አናገኝም በሚል ሞት ይፈረድባቸዋል። በዚህ መልኩ እውነተኞቹን የእግዚአብሔር ልጆች በመግደልና በማሳደድ ተግባር የሚጠመዱት ራሳቸውን ለሃይማኖታቸው ቀናዒ፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ፈጻሚ አድርገው በመውሰድ በሙሉ ልብ ለሚፈጽሙት ግፍ ማጣፊያ ለማቅረብ ይሞክራሉ።



### 4. የዳንኤልን እና የራዕይ መጻሕፍትን ስናጠና ሁልጊዜ ዋነኛው ጠላት ዲያብሎስ መሆኑን ነው የምንረዳው፤ ትክክል ነው?

ምንም ጥርጥር የለውም፤ የሁልጊዜ ጠላታችን ሰይጣን ነው፤ እርሱ ደግሞ የሚሠራው የምድር ነገሥታትን፣ መሪዎችንና ተጽዕኖ ፈጣሪዎችን በመጠቀም ነው። ይህንንም በማድረግ የእግዚአብሔርን ልጆች ይጎዳል፤ እስከ መግደልም ይደርሳል። በዚህ ድርጊቱ እግዚአብሔር አምላክንና ልጁን ጌታችን ኢየሱስን እንደሚጎዳ ያውቃል። ለማንኛውም ክፋት ሁሉ ተጠያቂው ሠይጣን ነው። ከተኮነነም በቅድሚያ መኮነን ያለበት እርሱ ነው እንጂ ሰዎች ወይም የሃይማኖትና የፖለቲካ መሪዎች አይደሉም። በግለሰቦች፣ በመሪዎች (የሃይማኖትም ይሁን የፖለቲካ)፣ በመሳሰሉ ሰዎች ላይ ጣት ከመቀሰር ልንጠነቀቅ ይገባል። አውቀውትም ይሁን ሳያውቁት መጠቀሚያ ሊሆኑ ይችላሉ። በዚህም ድርጊታቸው ሰዎችን ሲጎዱ ላያውቁት ይችላሉ። ሰይጣንን በተመለከተ ግን እንደዚህ አይደለም፤ እርሱ የሚሠራውን ጠንቅቆ ያውቃል። እግዚአብሔርንና ሕዝቡን ሲጎዳ ሆን ብሎ አስቦና አቅዶ ነው።

### 5. የርዕሳነ ሊቀጳጳስ ሞት ይሁን የአሜሪካ ፕሬዚዳንት መቀየር በራዕይ 13፡11-18 ትንቢት አፈጻጸም ላይ የሚያመጣው ለውጥ ይኖር ይሆን?

የመሪዎቹ መቀያየር በትንቢቱ አፈጻጸም ላይ የሚያመጣው ምንም ለውጥ የለም። ምናልባት የሰዎቹ ማንነት እና የግል ዕምነት ትንቢቱ እንዲፈጸም ሊያፋጥን ወይም ሊያዘገይ ይችላል። የትንቢቱ አፈጻጸም ግን መጽሐፍ ቅዱስ እንደተነበየው ነው የሚሆነው።

### 6. በራዕይ 13፡11-18 በግ መሰል አውሬ ተብሎ የተጠቀሰውና በራዕይ 16፡13 ሃሰተኛው ነቢይ የተባለው አንድ ናቸው?

አዎ አንድ ናቸው፤ በራዕይ 19፡20 አውሬው እና ሐሰተኛው ነቢይ ወደ እሣት ባሕር በመጣል እንደሚቃጠሉ ይናገራል። በዚሁ ምዕራፍ 19 ስለ ሃሰተኛው ነቢይ ሲናገር ተዓምራትን የሚያደርግ፣ ሰዎች የአውሬውን ምልክት እንዲቀበሉና ለምስሉም እንዲሰግዱ የሚያስታቸው እንደሆነ ይናገራል። በራዕይ 13፡11-18 በግ መሰል አውሬ ተብሎ የተጠቀሰውም ይህንኑ ሥራ እንደሚያደርግ እናነባለን። ስለዚህ በራዕይ 19 ሐሰተኛው ነቢይ ተብሎ የተጠቀሰውና በራዕይ 13 በግ መሰል አውሬ የተባለው አንድና ተመሳሳይ ናቸው። ዝዉ (ቅንብር፤ ጥበበሥላሴ መንግሥቱ)

# “እንደ ዘንዶ”

“ሌላም አውሬ ከምድር ሲወጣ አየሁ፥ የበግ ቀንዶችን የሚመስሉ ሁለት ቀንዶችም ነበሩት እንደ ዘንዶም ይናገር ነበር። በፊተኛውም አውሬ ሥልጣን በእርሱ ፊት ሁሉን ያደርጋል። ለሞቱ የሆነውም ቍስል ተፈወሰለት ለፊተኛው አውሬ ምድርና በእርሱ የሚኖሩት እንዲሰግዱለት ያደርጋል” (ራዕዩ 13፡11-12)።

የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢት እንደሚነግረን አሜሪካ በመጀመሪያ እንደ በግ ትጀምርና ቀጥሎ ግን “እንደ ዘንዶ” መናገር ትጀምራለች።

በራዕዩ 12፡9 እንደምናነበው ዘንዶ የሚያመለክተው ሰይጣንን ነው። ይኸው ምዕራፍ ሰይጣን እንዴት እንደሚሠራ በዝርዝር ሲያስረዳ በጣም ቁጡ፣ ጨካኝ እና አሰዳጅ ኃይል ነው ይለዋል (ቁጥር 4፣ 12፣ 13፣ 15፣ 17)። በጣም ጨካኝ በሆነው ኃይሉ ከፍተኛ ጥቃት ይሰነዝራል፤ እግዚአብሔርን ፈጽሞ ስለሚጠላ ተከታዮቹንም እንዲሁ ይጠላቸዋል። ዓላማው በፊት እንደነበረው አሁንም ያው ነው፤ ይኸውም የእግዚአብሔርን ዙፋን በመንጠቅ ሰዎች ሁሉ እርሱን እንዲያመልኩና እንዲታዘዙ በግድ ማድረግ ነው (ኢሳይያስ 14፡12-14)።

አንድ መንግሥት እንዴት “ይናገራል” ብለን ከጠየቅን መልሱ በሚያወጣው ሕግና በሚነድፈው ፖሊሲ የሚለው ይሆናል። ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ “እንደ ዘንዶ ይናገራል” ሲል አሜሪካ ሕግ በማውጣትና ፖሊሲ በመተግበር የሰይጣንን ፍላጎት ያሳካል ማለት ነው።

በእርግጥ ይህ የሚያስደነግጥ ነገር ሊሆን ይችላል። እንዴት ነው እንደ አሜሪካ ያለ የነጻት አገር ይህንን የመሰለ አደገኛና አፋኝ ነገር የሚያደርገው ብለን ልንጠይቅ እንችላለን። እስቲ አሜሪካንን የሚወክለው ሁለተኛውን አውሬ በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረውን በጽሞና እንከታተል፤

1. “በፊተኛውም አውሬ ሥልጣን በእርሱ ፊት ሁሉን ያደርጋል” (ራዕዩ 13፡12)። እንደ ጳጳሳዊው ሮም አሜሪካም ውሎ አድሮ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የማይስማማ እና ግለሰባዊ የኅሊና ነጻነትን የሚገፍ አምልኮ እንዲተገበር አሰዳጅ ኃይል ይሆናል። በሌላ አነጋገር ሰዎች በግድ የሆነ እምነት እንዲከተሉ ያደርጋል።

2. “ለሞቱ የሆነውም ቍስል ተፈወሰለት ለፊተኛው አውሬ ምድርና በእርሱ የሚኖሩት እንዲሰግዱለት ያደርጋል” (ራዕዩ 13፡12)። አሜሪካ ለእርሷ እንዲሰገድላት የምታደርግ ሳይሆን ከዚያ ይልቅ በዓለም የሚኖሩ ሁሉ ለመጀመሪያው አውሬ ወይም ለሐሰዊው መሢሕ ወይም ለጳጳሳዊው ኃይል እንዲሰግዱ ታስገድዳለች።

3. “የሰይፍም ቍስል ለነበረውና በሕይወት ለኖረው ለአውሬው ምስልን እንዲያደርጉ በምድር የሚኖሩትን ይናገራል” (ራዕዩ 13፡14)። ምስል ማለት የአካሉ ወይም የዋናው አምሳያ ማለት ነው። የፊተኛው አውሬ ምስል ማለት የጳጳሳዊ ሥርዓትን የሚወክል በሌላ አነጋገር የእርሱን ገጽታ ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ምስል ማለት ነው። ስለዚህ አሜሪካ የጳጳሳዊ ሥርዓትን ምስል ለማቆም በቅድሚያ መሠረታዊ የሆነውን እና በቤተክህነትና በቤተመንግሥት መካከል ያለው ልዩነት በማስወገድ ሁለቱን ማዋኻድ አለባት። ይህንን በምታደርግበት ጊዜ ጳጳሳዊው ሥርዓት በጨለማው ዘመን እጅግ ገንኖ የነበረው ሥልጣኑ እንዲመለስ የሚያደርጉ ሃይማኖታዊ ሕግጋትን በማውጣትና በመተግበር ምስል የማቆም ሥራዋን ትፈጽማለች። ከዚያም ዓለም ሁሉ የእርሷን ፈለግ በመከተል ተመሳሳይ ነገር እንዲያደርግ ተጽዕኖ ታሳድራለች።

4. “የአውሬው ምስል ሊናገር እንኳ ለአውሬውም ምስል የማይሰግዱለትን ሁሉ ሊያስገድላቸው፥ ለአውሬው ምስል ትንፋሽ እንዲሰጠው ተሰጠው” (ራዕዩ 13፡15)። በጨለማው ዘመን ጳጳሳዊው ሥርዓት በእምነታቸው ምክንያት በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎችን እንደገደለ ሁሉ አሜሪካም ተጽዕኖ የማድረግ ብቃቷን ተጠቅማ ለአውሬው ወይም ለምስሉ አንሰግድም በማለት በሚጸኑ ሁሉ ላይ የሞት ዓዋጅ ታውጃለች።

“አንባቢው ያስተውል”

“እነዚህ ነገሮች መፈጸም ሲጀምሩ፣ መዳናችሁ ቀርቦአልና፤ ራሳችሁን ወደ ላይ ቀና አድርጉ” (ሉቃስ 21፡28)።



REMEMBERING

# Dr. Roland Kazen

***Giziew magazine*** lovingly remembers Dr. Roland Kazen, whose 14 years in Ethiopia were a testament to the power of selfless love. As an orthopedic and leprosy surgeon, Dr. Kazen's hands became instruments of healing and hope. He didn't just treat disease—he restored dignity, often in the face of overwhelming despair. For those who felt forgotten by the world, he was a beacon of compassion. His patients were not just cases to him; they were souls deserving of care, and his gentle presence brought light to their darkest moments.

But Dr. Kazen's gifts extended beyond the operating room. A skilled musician, he filled the air with melodies from the organ and flute, leading choirs at Filowah Seventh-day Adventist Church with the same passion that he devoted to his medical work. His music was a reflection of the beauty he saw in life, even amidst suffering.

To know Dr. Kazen was to witness a rare and profound kindness, a wisdom that seemed to flow effortlessly from a heart fully committed to others. Though his voice is now silent and his hands at rest, the echoes of his life continue to resonate in the hearts of all who were blessed to know him. He is deeply missed, yet the love he gave remains, etched in the lives he touched forever.